# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

83ኛ ዓመት ቁጥር 046 ጥቅምት 16 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)

የሁሉም ባንክ
Bank for all !

የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ !

በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia








ፎቶ፡ አዩብ ተፈሪ እና በረሀን ታደሰ

# «ኢትዮጵያ በኃይልና በወረራ ማሳካት የምትፈልገው አንዳች ነገር የለም»

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)


ገጽ 6










# መከላከያ

## ታሪኩንና አንድነቱን ጠብቆ የሚጓዝ ጽኑ ተቋም ነው

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት ታሪኩንና አንድነቱን ጠብቆ የሚጓዝ ጽኑ ተቋም ነው ሲሉ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ ገለጹ።

"በተፈተነ ጊዜ ሁሉ የሚፀና የድል ሠራዊት" በሚል መሪ ሃሳብ 116ኛው የሠራዊት ቀን በመስቀል አደባባይ


መከላከያ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል


# ከኦሮሚያ

## የተፈናቀሉ ዜጎች መልሶ የማቋቋም እንቅስቃሴ ተጀምሯል


ገጽ 6


# «ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ መድረኮች የገባቻቸውን ቃል ኪዳኖች በቁርጠኝነት እየፈጸመች ነው»

- አቶ ደመቀ መኮንን
ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር

**አዲሱ ገረመው**

ቢሾፍቱ፡- ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ መድረኮች የገባቻቸውን ቃል ኪዳኖች በቁርጠኝነት እየፈጸመች መሆኗን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን ገለጹ።

የኢትዮጵያ መንግሥት የስደተኞችና ተቀባይ ማኅበረሰቦችን ሕይወት ለማሻሻል ስድስት ቃል ኪዳኖችን ትላንት ባፀደቀበት ጉባኤ ላይ አቶ ደመቀ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ፈተናዎች ውስጥም ሆና በሚሊዮን የሚቆጠሩ ስደተኞችና ጥገኞችን ተቀብላ ማስተናገድ ችላለች።

ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ዐውድ ውስጥ ልዩ ልዩ ኃላፊነቶችን እየተወጣች፣ የገባቻቸውን ቃል ኪዳኖችም በቁርጠኝነት እየፈጸመች ነው ያሉት ሚኒስትሩ፣ ከዓለም


«ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል












አሳምነው ተሾመ (ዶ/ር)

## ወቅቱን ባልጠበቀ ዝናብ የደረሱ አዝርዕት እንዳይበላሹ ትኩረት እንዲሰጥ ኢንስቲትዩቱ አሳሰበ

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- በመኸር ወቅት ተዘርተው በመድረስ ላይ በሚገኙ አዝርዕት ወቅቱን ባልጠበቀ ዝናብ እንዳይበላሹ ትኩረት ተሰጥቶ እንዲሠራ የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አሳሰበ።

በኢንስቲትዩቱ የሚቲዎሮሎጂ ትንበያና ቅድመ ማስጠንቀቂያ ምርምር ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አሳምነው ተሾመ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የተሰጠውን ትንበያ መሠረት በማድረግ የደረሱ አዝርዕትን ለመሰብሰብ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል።

የበጋ ወቅት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የአየር ንብረት ሁኔታው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ሊያስከትል እንደሚችል በተሰጠው ትንበያ መሠረት የደረሱ ሰብሎችን መሰብሰብ ይገባል ብለዋል።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ በበጋ ወቅት አብዛኛው አካባቢዎች አልፎ አልፎ ከሚፈጠሩና ከሚጠናከሩ የአየር ንብረት ክስተቶች በመነሳት ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ሊከሰት ይችላል። በዘንድሮ የበጋ ወቅት በተተነበየው መሠረት ሁለተኛው የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑ አካባቢዎች ከመደበኛው በላይ የሆነ የዝናብ ሁኔታ ይኖራቸዋል።

ለደቡብ አጋማሽ አካባቢዎች ለሶማሌ ክልል ደቡባዊ ክፍል፣ ለጉጂ፣ ለቦረና፣ ለሲዳማ ክልል፣ ለጋሞ፣ ለጎፋና ለተወሰኑ ደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች ከመደበኛ በላይ የዝናብ ሁኔታ የሚኖርበት ምክንያት የሕንድ ውቅያኖስ ምዕራባዊ ክፍሉ ከመደበኛ በላይ የመሞቅ አዝማሚያ ስለሚያሳይ መሆኑንም ነው ያብራሩት።

ይህ በሚሆንበት ጊዜ በደቡብ አጋማሽ አካባቢዎች ላይ የተስፋፋና የተጠናከረ የዝናብ ሁኔታ ይኖራል። ከዚህ ጋር ተያይዞም ከመደበኛው በላይ ዝናብ እንደሚያገኙ ትንበያ ተሰጥቷል ነው ያሉት።

በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑ ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የተለያዩ የግብርና አካባቢዎችን ለማከናወን፣ የመጠጥ ውሃን እና ለእንስሳት መኖን ከማሻሻል አኳያ ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር፣ በአንጻሩ ግን ዝናብ ለማያገኙ አካባቢዎች ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ እንደሚኖርም ነው የጠቀሱት።

በተለይም ከሚቀጥሉት ቀናት ጀምሮ በአብዛኛው የአገሪቱ አካባቢዎች የደመና ሽፋን ይጨምራል። በብዙ የአገሪቱ አካባቢዎች ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ሊከሰት እንደሚችል አመላካች ሁኔታ አለ። በመሆኑም ተገቢና አስፈላጊ ጥንቃቄ ሊደረግ እንደሚገባ ነው ያሳሰቡት።

በመስኖ ለሚሠሩ የግብርና እንቅስቃሴዎች ወቅቱን ያልጠበቀው ዝናብ ፋይዳ ሊኖረው እንደሚችል የገለጹት አሳምነው (ዶ/ር)፤ ባግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል ዝግጅት መደረግ እንዳለበትም መክረዋል።

የበጋው ወቅት አብዛኛው አካባቢዎች ለትግራይ፣ ለአማራ፣ ለአፋር፣ አብዛኛው ኦሮሚያ፣ ለጋምቤላ፣ ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች ደረቅ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ እንደሚያመዝንም ተናግረዋል።

በአንጻሩ ለደቡብ አጋማሽ አካባቢዎች ለሶማሌ ክልል ደቡባዊ ክፍል፣ ለጉጂ፣ ለቦረና፣ ለሲዳማ ክልል፣ ለጋሞ፣ ለጎፋና ለተወሰኑ ደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች እንደሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ተደርጎ ይወሰዳል። ከዓመታዊ የዝናብ ወቅት ለእነዚህ አካባቢዎች ከ45 በመቶ የሚገኘው በበጋ ወቅት መሆኑንም ነው ያስገነዘቡት።

# የሲዳማ ክልል ከ68 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በበጋ መስኖ ሊያለማ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የሲዳማ ክልል ከ68 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በበጋ መስኖ ለማልማት የዝግጅት ሥራዎች እያከናወነ መሆኑን የክልሉ የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ አስታወቀ።

የሲዳማ ክልል የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ መምሩ ሞኬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ክልሉ በዘንድሮ የበጋ መስኖ ልማት ከአምናው የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ከአሁኑ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን እያከናወነ ነው። በዚህም ክልሉ በዘንድሮ በበጋ መስኖ ከ68 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት ለማልማት እየሠራ ነው።

ክልሉ በዘንድሮ በጋ መስኖ ልማት ስንዴ፣ ሽንኩርት፣ ቲማቲም እና ሌሎች አትክልቶችን ያለማል ያሉት አቶ መምሩ፤ በሁለት ዙር ከ68 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት የሚለማ ሲሆን በመጀመሪያው ዙር 55 ሺህ ሄክታር መሬት ይለማል። በሁለተኛው ዙር ደግሞ 13 ሺህ ሄክታር መሬት ይለማል። ከአጠቃላይ 68 ሺህ ሄክታር መሬት የበጋ መስኖ ስንዴ ሁለት ሺህ 750 ሄክታሩን ይሸፍናል ብለዋል።

እንደ አቶ መምሩ ገለፃ፤ በክልሉ የበጋ መስኖ ስንዴ፣ ጥቅል ጎመን፣ ካሮት፣ ቀይ ሥርና ቲማቲም በስፋት ይለማሉ። ምርቱንም በሦስት ወር ውስጥ መሰብሰብ ይቻላል። በዘንድሮ ከግብዓት አቅርቦት እና ከምርጥ ዘር ጋር የነበሩ ችግሮችን ለመፍታት ከአሁን ጀምሮ የሚሠራ ይሆናል።

ከአምናው የበጋ መስኖ የተገኙ ልምዶችና ተሞክሮዎችን በዘንድሮ ዓመት ለማጠናከር አሁን ላይ በርካታ ሥራዎች ለመሥራት በቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ላይ ነን ብለዋል።

ባለፉት ሁለት ዓመታት ወቅቱን የጠበቀ ዝናብ አልነበረም። ሆኖም ክልሉ ባለፉት ዓመታት የበጋ መስኖ ልማት ላይ ሰፊ ትኩረት አድርጎ ሲንቀሳቀስ ቆይቷል። በተለይ መንግሥት ከበጋ መስኖ ስንዴ ጋር ተያይዞ የውሃ መሳቢያ ፓምፕ፣ ምርጥ ዘር አቅርቦት እና ለአርሶ አደሩ ግንዛቤ ፈጥሯል። ይህም ለሲዳማ ክልል የበጋ መስኖ ልማት በስፋት እንዲለማ አስቻሏል ሲሉ ገልጸዋል።



አቶ መምሩ ሞኬ

ባለፉት ዓመታት የበጋ ስንዴ አምርተው በማያውቁ አካባቢዎች ላይ በግንዛቤ ማነስ ምክንያት አርሶ አደሩ ወደ ልማቱ ለመግባት የቁርጠኝነት ማነስ ችግር እንደነበረበት ያነሱት አቶ መምሩ፤ የመስክ ምልከታ በማድረግ ችግሮቹን ለመፍታትና በዘንድሮ ዓመት በቂ ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ከፍተኛ ምርት ለማግኘት ታቅዷል ብለዋል።

በየአካባቢው ያሉ የውሃ አማራጮችን ከወዲሁ በመለየት ለቀጣይ ዓመት የውሃ አቅምን አሟጦ በመጠቀም የበጋ መስኖ ስንዴ ልማቱን ለማስፋፋት ዝግጅት እየተደረገ መሆኑንም አቶ መምሩ ገልጸዋል።




አቶ ፀጋዬ አማኑኤል

# ኢትዮ ቴሌኮም

## የሳይበር ጥቃትን ለመከላከል በትኩረት እየሠራ ነው

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮ ቴሌኮም የሳይበር ጥቃትን ለመከላከል በርካታ ሥራዎችን እየሠራ መሆኑን ገለጸ።

በየዓመቱ በጥቅምት ወር የሚከበረውን የሳይበር ደህንነት ወር ኢትዮ ቴሌኮም ለሦስተኛ ጊዜ ትናንት ከገንዘብ ተቋማትና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር አክብሯል።

የኢትዮ ቴሌኮም ቺፍ ኢንፎርሜሽን ኦፊሰር አቶ ፀጋዬ አማኑኤል በመድረኩ ባደረጉት ንግግር፤ ኢትዮ ቴሌኮም የሳይበር ደህንነትን ለማስጠበቅ በርካታ ሥራዎችን እየሠራ ነው። በዋናነትም ደንበኞችን የማሳወቅ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል።

የሳይበር ደህንነት ስጋት ሰዎች ዲጂታል አገልግሎትን እንዳይጠቀሙ የሚያደርግ በመሆኑ ተቋሙ ይህንን ተገንዝቦ እየሠራ መሆኑን ለደንበኞች ግንዛቤ ለማስጨበጥ ሥራ ተሠርቷል ብለዋል ኃላፊው።

በቴሌብር 38 ሚሊዮን ደንበኞችን በማፍራት በሁለት ዓመታት ውስጥ ከአንድ ነጥብ ሦስት ትሪሊዮን ብር በላይ የገንዘብ ዝውውር መደረጉን የጠቆሙት ኦፊሰሩ፤ የቴሌብር ሲስተም የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ደህንነቱን በማስጠበቅ ላይ መሆኑን ገልጸዋል።

የቴሌብር አጠቃቀምን ለደንበኞች ደህንነት ሲባል ሲምካርድ መጠቀም አስፈላጊ እንዲሆን መደረጉን የጠቆሙት አቶ ፀጋዬ፤ ተጠቃሚ የሳይበር ደህንነት ግንዛቤ እንዲያድግ በአጭር የጽሑፍ መልዕክትና በተለያዩ መንገዶች በመጠቀም የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑንም አመላክተዋል። የሳይበር ጥቃትን ሁልጊዜ ሊከሰት ይችላል በሚል በጥንቃቄ መከላከል ላይ መሥራት እንደሚያስፈልግም አክለው ገልጸዋል።

ኢትዮ ቴሌኮም የሳይበር ደህንነትን ለማስጠበቅ በብሔራዊ ደረጃ በሳይበር ደህንነት ላይ እየሠራ ከሚገኝ ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ጋር በጋራ እንደሚሠራ የተጠቆመ ሲሆን ከሌሎች የገንዘብ ተቋማት ጋርም የልምድ ልውውጥ እንደሚያደርግ ተነግሯል።

በማንኛውም ሰዓት ደንበኞች የሳይበር ጥቃት ሊያጋጥማቸው እንደሚችል የተናገሩት አቶ ፀጋዬ፤ ደንበኞች የተረጋገጡ መተገበሪያዎችን ብቻ በጥንቃቄ በመጫን መጠቀም እንዳለባቸውና ተመሳስለው የተሠሩ መተግበሪያዎችን መጠቀም እንደሌለባቸው አሳስበዋል።

“የኢትዮ ቴሌኮም እና የባንክ ሠራተኞች ነን” ብለ ለመርዳት በማስመሰል በሚደውሉ ሰዎች እንዳይታለሉና ምንም አይነት የገንዘብ ዝውውር እንዳያደርጉ አስጠንቅቀዋል።

ዜና

# ለሌማት ትሩፋት ግብዓት የሚውል 30 ሚሊዮን ዶላር ተመደበ



**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

አዲስ አበባ፡- ለሌማት ትሩፋት መርሐ ግብር ስኬት ባለሀብቶች የሚገጥማቸውን የውጭ ምንዛሪ ችግር ለመቅረፍ በተያዘው በጀት ዓመት 30 ሚሊዮን ዶላር በብሔራዊ ባንክ በኩል መመቻቸቱን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።

በግብርና ሚኒስቴር የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት መሪ ሥራ አስፈጻሚ ወይዘሮ ጽጌሬዳ ፍቃዱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ የግብርና ግብዓት አስመጪ ባለሀብቶች የሚገጥማቸውን የውጪ ምንዛሪ ችግር ለመፍታት የተፈቀደላቸውን በጀት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መጠቀም ጀምረዋል። የውጪ ምንዛሪ መመቻቸቱ በግብዓት አቅርቦት እጥረት ሳቢያ በመርሐ ግብሩ አፈጻጸም ላይ የሚፈጥረውን ጫና በከፍተኛ ሁኔታ ይቀንሳል።

በየጊዜው እያደገ የመጣውን የእንስሳት ተዋፅዖ ምርታማነት ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሳደግ ትልቅ ፋይዳ እንደሚኖረውም ገልጸዋል።

እንደ ሥራ አስፈጻሚዋ ገለጻ፣ ባለፈው ዓመት ጥቅምት ወር በአርባ ምንጭ ከተማ ጠቅላይ ሚኒስትሩና የክልል ርዕሰ መስተዳድሮች በተገኙበት በተጀመረው የሌማት ትሩፋት መርሐ ግብር በዚያው ዓመት ሦስት ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን እንቁላል መመረት ችሏል። በተያዘው ዓመት ይህንን ቁጥር ከስድስት ቢሊዮን በላይ ለማድረስ እየተሠራ ነው።

ባለፈው ዓመት 42 ሚሊዮን የአንድ ቀን የዶሮ ጫጩት መሰራጨቱን ያስታወሱት ኃላፊዋ፤ በአሁኑ ጊዜ ስርጭቱን ወደ 62 ሚሊዮን ለማሳደግ ታቅዷል ሲሉ አብራርተዋል።

በያዝነው በጀት ዓመት ሩብ ዓመትም ሦስት ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ሊትር ወተት፣ 24 ሺህ ቶን የዶሮ ሥጋ፣ አንድ ነጥብ 28 ቢሊዮን እንቁላል፣ 14 ሺህ ቶን ዓሣ፣ ዘጠኝ ነጥብ አምስት ሚሊዮን የዶሮ ጫጩት ማምረት እንደተቻለ ወይዘሮ ጽጌሬዳ ተናግረዋል።

መርሐ ግብሩ በመንደር እንዲሠራ በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት የየአካባቢውን የማምረት አቅም በማየት የዶሮ፣ የንብ፣ የወተት፣ የዓሣ እና ሌሎችም መንደሮችና ተጠቃሚ ቤተሰብ የመለየት ሥራ መሠራቱን የጠቀሱት ሥራ አስፈጻሚዋ፤ ከዚህም ውስጥ በአራት ዓመታት ውስጥ 27 ሺህ የዶሮ መንደሮች ለመለየት ታቅዶ ዘጠኝ ሺህ የዶሮ መንደሮችን መለየት እንደተቻለም ገልጸዋል። መንደር የመለየት፣ አምራች ወጣቶችን የማደራጀትና የማሠልጠን ሥራ ቀጣይነት ኖሮት እየተሠራ እንደሆነም አያይዘው ጠቁመዋል።

ወይዘሮ ጽጌሬዳ እንዳሉት፤ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ለሚገጥሙት ችግሮች መፍትሔ እየሰጠ በሁሉም ምርቶች የመርሐ ግብሩን ውጤታማነት ለማሳደግ እየሠራ ያለ ሲሆን፣ በይበልጥ ለወተት ምርት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት እስከያዝነው ዓመት መጨረሻ ድረስ ዘጠኝ ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ሊትር ወተት ለማማረት እቅድ ይዟል።



# ኢትዮጵያ ለውጭ ገበያ የምታቀርበው የማር ምርት ቅናሽ እያሳየ መጥቷል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ባለፉት 11 ዓመታት ለውጭ ገበያ የምታቀርበው የማር ምርት ቅናሽ እያሳየ መምጣቱን ግብርና ሚኒስቴር ገለጸ።

በግብርና ሚኒስቴር የንብ ሀብት ልማት ዴስክ ኃላፊ አቶ አዚዝ አያሌው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለፉት ሰባት ዓመታት የንብ ልማትና ከንብ የሚገኘው ምርት እያደገ ቢሄድም ለውጭ ገበያ የሚቀርበው የማር ምርት ቅናሽ እያሳየ መጥቷል።

ኢትዮጵያ በ2003 በጀት ዓመት 896 ቶን የማር ምርት ለውጭ ገበያ ማቅረቧን አውስተው፤ በ2014 በጀት ዓመት ለውጭ የተላከው የማር ምርት ወደ 50 ቶን ዝቅ ማለቱንና በ2015 በጀት ዓመት ደግሞ ከዚህም ዝቅ ያለ መሆኑን ገልጸዋል።

አቶ አዚዝ የማር ምርት ላይ የውጭ ምንዛሪን ግኝትን ለማሳደግ ታስቦ እየተሠራ ቢሆንም፤ በሀገር ውስጥ ያለው ዋጋ ውጭ ካለው ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ በመሆኑ በዘርፉ የተሰማሩ ነጋዴዎች ማርን ወደ ውጭ ከመላክ ይልቅ በሀገር ውስጥ መሸጥን ተመራጭ ያደርጋሉ ብለዋል።

ለዋጋ ልዩነቱ ዋነኛዎቹ ምክንያቶች ወደ ውጭ ሀገራት የሚላክ ማር ጥራቱን የጠበቀ መሆን ስለሚኖርበት አስፈላጊውን ምርመራ የሚደረግለት መሆኑን አመልክተው፤ በሀገር ውስጥ ያለው የንግድ ሥርዓት ማርን ከሌላ ነገር ጋር ቀላቅለው ሲሸጡ ጠያቂ ባለመኖሩ በዘርፉ በወጪ ንግድ ተሰማርተው የሚገኙ ነጋዴዎች ለውጭ ገበያ ሳያቀርቡ ስማቸውን እየቀየሩ ምርቱን ሀገር ውስጥ እየሸጡ መሆኑን ገልጸዋል።

ሌላኛው በዘርፉ ላይ ያለው ችግር በድንበር አካባቢ ሕገወጥ የማር ንግድ መኖሩን ጠቁመው፤ ይህም ወጪ ንግዱ ቅናሽ እንዲያሳይ ማድረጉን ጠቅሰዋል። በዚህም ለውጭ የሚቀርብ የማር ምርት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ እንዲሄድ ምክንያት መሆኑን ተናግረዋል።

አቶ አዚዝ፣ በቀጣይ የማር ምርት የውጭ ምንዛሪ ከሚገኙባቸው ምርቶች መካከል ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን ገልጸው፤ እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ አቅጣጫዎች መቀመጣቸውንና ሕገ ወጥ ንግዶችን ለማስቆም አዋጅና ደንቦች በማውጣት ወጥ የሆነ አሠራር እንዲኖር ለማስቻል እየተሠራ ይገኛል ብለዋል።

ኢትዮጵያ በዓመት 500 ሺህ ቶን ማር የማምረት አቅም ቢኖራትም ንብ የማነብ ዘዴ አብዛኛው ባሕላዊ በመሆኑ እየተጎዳች ነው ብለዋል።

በ2015 በጀት ዓመት የተመረተው ማር 193 ሺህ ቶን መሆኑን በማንሳትም፤ በ2016 በጀት ዓመት ደግሞ 217 ሺህ ቶን ማር ለማምረት መታቀዱን ዴስክ ኃላፊው ገልጸዋል።

ይህንን ለማሳካት መንግሥት ንብን ለማነብ የሚያግዙ የተለያዩ ግብዓቶችና ቴክኖሎጂዎች ያለቀረጥ እንዲገቡ መፍቀዱንና ይህም በቀጣይ በማር ምርትና በወጪ ንግድ ገቢ ላይ መሻሻል ያመጣል ተብሎ እንደሚጠበቅ አመልክተዋል።

# አራት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን የመማሪያ መጽሐፍት ለመዲናዋ ትምህርት ቤቶች እየተሰራጩ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**



አቶ ወንድሙ ዑመር

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ አራት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን የመማሪያ መጽሐፍት ለትምህርት ቤቶች እየተሰራጨ መሆኑን የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ አስታወቀ። ቢሮው በያዝነው ወር መጨረሻ የመጽሐፍት አቅርቦት ችግርን ሙሉ ለሙሉ ለመፍታት እየሠራ መሆኑንም ገልጿል።

የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ወንድሙ ዑመር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ቢሮው ስድስት ሚሊዮን መጽሐፍት ለማሳተም ከአታሚ ድርጅቶች ጋር ተዋውሏል። እስከ አሁን አራት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን የመማሪያ መጽሐፍት የታተሙ ሲሆን ይህም ለትምህርት ቤቶች እየተሰራጨ ይገኛል።

በከተማ ደረጃ ስድስት ሚሊዮን መጽሐፍት ታትመው እንዲሠራጩ እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ ከዚህ ውስጥ ከአራት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን በላይ የመምህራን መምሪያ እና የተማሪ መማሪያ መጽሐፍት ታትመው ለትምህርት ቤቶች እየተሰራጩ እንደሆነ ተናግረዋል።

በቀጣይ ሁለት ሳምንታት ደግሞ ቀሪዎቹ አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን የመማሪያ መጽሐፍት ለሁሉም ትምህርት ቤቶች የሚሰራጩ ይሆናል። ኅብረተሰቡ ከመጽሐፍ ስርጭት ጋር ተያይዞ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች ተገቢ መሆኑን ገልጸው፤ የመጽሐፍት አቅርቦት ችግሩ ያጋጠመው አዲስ ሥርዓተ ትምህርት ተግባራዊ እየተደረገ በመሆኑ ነው ብለዋል።

አዲስ ሥርዓተ ትምህርት ተግባራዊ ሲደረግ አዲስ በጀት፣ መጽሐፍት መቀየር፣ መምህራንን ማሠልጠን ያስፈልጋል ያሉት አቶ ወንድሙ፤ አሁን ሀገሪቱ የሥርዓተ ትምህርት ሽግግር ላይ ነች። ይህ ደግሞ ጊዜ ይፈልጋል።

እንደ አቶ ወንድሙ ገለፃ፤ ባለፈው ዓመት አዲሱ ሥርዓተ ትምህርትን ተግባራዊ ለማድረግ የተለያዩ ሙከራዎች ተደርገዋል። በዚህም የተወሰኑ ክፍተቶች ተስተውለዋል። በተለይ በመማሪያ መጽሐፍ እጥረቱ በኩል የኅትመት መጓተት፣ የኅትመት ዘርፉ የአቅም ማነስ፣ የአታሚዎች ውል አለማክበር እና መምህራን መጽሐፍቱ ላይ ማስተካከያ እንዲደረግ ጥያቄ ማቅረባቸው የመጽሐፍት ስርጭቱ እንዲዘገይ አድርጎታል።

ቢሮው ይህን ችግር ለመፍታት መጽሐፍቱ እየታተሙ ከስር ከስር ለትምህርት ቤቶች እንዲደርሱ እየሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ በሂደት ላይ ትምህርት ቤቶች ለማስተማር ችግር እንዳይገጥማቸው ሶፍት ኮፒ እንዲደርስ ተደርጓል ብለዋል።

በቀጣይ ሁለት ሳምንታት የመጽሐፍቱ ኅትመት ሙሉ በሙሉ ተጠናቆ ለትምህርት ቤቶች ለማሰራጨት እየተሠራ መሆኑንም ተናግረው፤ አንዳንድ የግል ትምህርት ተቋማት አዲሱን ሥርዓተ ትምህርት በትክክል በመተግበር በኩል ክፍተት መስተዋሉን ያስታወሱት አቶ አድማሱ፤ ማስተካከያ የማያደርጉ ከሆነ ሕጋዊ ርምጃ እንደሚወሰድባቸው ገልጸዋል።

አዲሱን ሥርዓተ ትምህርት ለመተግበር በሚደረገው ጥረት ውስጥ ሁሉም ነገር በአንድ ጊዜ ላይሟላ እንደሚችል ገልጸው፤ መጽሐፍቱ ላይም አልፎ አልፎ የሚነሱ አስተያየቶች ስላሉ ይህንን አስተካክሎ መሄድ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው ብለዋል።

በመሆኑም በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይም ሆነ በመጽሐፍቱ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎች ካሉ ቢሮው ለማስተካከል ዝግጁ መሆኑን በመጠቆም ማንኛውም ሰው ጥያቄውን ማቅረብ እንደሚችል ጨምረው ገልጸዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## መከላከያ የሀገር መከታ፣ የሕዝብም መመኪያ ነው !

የኢትዮጵያ ስምና ገጽታ ደምቆ ከሚገለጽባቸው አቅሞች መካከል አንዱ የመከላከያ ተቋምና የመከላከያ ሠራዊቱ ነው።ይሄ ተቋምና ሠራዊት በታሪክ ሂደት ሳይለዋወጥ፤ በሥርዓት ለውጥ ሳይለወጥ 116 ዓመታትን በብቃትም በጽናትም የሀገር ጠበቃና ኩራት ምንጭ ሆኖ የዘለቀ ነው።ዳግማዊ አፄ ምኒልክ በ1900 ለመጀመሪያ ጊዜ የኢትዮጵያን የጦር ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ማቋቋም እና ለተቋሙም ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ (አባ መላ) ኃላፊ/ሚኒስትር  አድርገው መሾም የተቋሙም፣ የሠራዊቱም አይለዋወጤነት መሠረት እንዲይዝ ያደረገ ነበር፡፡

በዚህም በተፈተነ ጊዜ ሁሉ የሚጸና የድል ሠራዊት መሆኑን ከ1900 እስከ 2016 ዓ.ም ባሉ 116 ዓመታት አሳይቷል።ይሄ እየተፈተኑ መጽናት፤ እየጸኑ ማሸነፍና ድል ማድረግ ታዲያ እንደ ትናንቱ ዛሬ፤ እንደ ዛሬውም ነገ ጸንቶ የሚቀጥል የመከላከያ ሠራዊቱ ታላቅ ተልዕኮ ነው።ይሄ ተልዕኮ ደግሞ ሀገራዊውን እውነት አውቆ፤ ዓለምአቀፋዊውን ሁነት ተገንዝቦ ለሁሉም በሁሉም ቦታ መገኘትን፤ አለኝታና ጋሻ፣ የሠላምና ደኅንነት ዋስትና መሆንን በተግባር መግለጥን አጠናክሮ ማስቀጠልን የሚሻ ነው፡፡

መከላከያ ከምንም በላይ የሠላም ኃይል ነው።ይሄ የሠላም ኃይልነቱ ደግሞ አንድም ያለን ነገር እንዳይጠፋ በማድረግ ውስጥ ይገለጻል።ሁለተኛም ከእጃችን ያመለጠንና ያጣነውን ሠላም በመመለስ ውስጥ ይገለጻል።ሦስተኛም፣ የመጣ ሠላምን በማጽናት ውስጥ የሚገለጽ ነው።እነዚህን ሦስት ነገሮች ማለትም፣ በእጅ ያለ ሠላም እንዳያመልጥ በማድረግ፤ ያመለጠ ሠላም እንዲመለስ በማድረግ፣ እንዲሁም የመጣ ሠላም ጸንቶ እንዲኖር በማድረግ ሂደት ውስጥ በሚገለጸው የሠላም ኃይልነት ውስጥ መከላከያ ሠራዊቱ ከፍ ዋጋ እየከፈለ ይገኛል፡፡

እነዚህ ደግሞ ትናንት ሲያደርጋቸው የነበረ፤ ዛሬም እያደረጋቸው፤ ነገም በልበ ሙሉነት የሚፈጽማቸው የእሱነቱ መሠረቶች ናቸው።ምክንያቱም ሠላምን መጠበቅ፣ መመለስና ማጽናት እንደ ትናንቱና ዛሬው ሁሉ ለነገ ብርቱ ትግልን ይሻል።ምክንያቱም፣ ሠላም ከወትሮው በተለየ ፈተናዋም፣ ፈታኟም በርክቷል፤ በርትቷልም።ይሄ የሠላም ጸር ኃይል ደግሞ በጊዜውና በሁኔታው ውስጥ ራሱን እየቃኘና እያስማማ ለመሄድ እረፍት የሌለው ፀረ ሕዝብና ሀገር ስብስብ ነው፡፡

መከላከያ ደግሞ ይሄንን ፀረ ሕዝብና ሀገር ስብስብ አደብ በማስያዝ፤ ሀገር እንድትረጋጋ፣ ሉዓላዊነቷ ተከብሮ እንድትዘልቅ፤ ዜጎችም ሠላምና ደኅንነታቸው ተጠብቆ ለሁለንተናዊ ብልጽግናቸው እንዲተጉ ያለ እረፍት ላብና ደም እያፈሰሰ፤ ሕይወቱን እየገበረ ዘብ የቆመ ኃይል ነው።በውስጥ ሆነው ሀገር የሚያምሱ ቡድኖችን በዱር በገደሉ ገብቶ አደብ የሚያስይዝ፤ ከውጭ ሆነው ኢትዮጵያን ሉዓላዊነቷን ለመዳፈር የሚቋምጡ ኃይሎችን ደግሞ በድንበሯ ላይ ቆሞ አጥር ሆኖ የሚያስከብራት ነው፡፡

ከዚህም ባሻገር እንደ ሀገር ጎረቤቶች ሠላም ሲያጡ፤ የዓለም ሀገራት በጦር ሲናጡ ደጀን ሆኖ የደረሰ፤ ለሠላማቸው አለኝታነቱን እያረጋገጠ የዘለቀ ኃይል ነው።በዚህም የሥርዓቶች መለዋወጥ እሱነቱን ያልለወጡት፤ የሀገሩንም ሠላምና ሉዓላዊነት አስጠብቆ፤ የሌሎችንም ሠላምና ደህንነት ከማስጠበቅ አኳያ የተሰጠውን ግዳጅ ከሩቋ ኮሪያ እስከ ጎረቤቷ ሶማሊያ በብቃት እየፈጸመ ያለ የሀገርም የወገንም ኩራት ነው፡፡

በፈተና ውስጥ እየጸና፤ በመጽናት ውስጥ እያሸነፈ በድል ከትናንት ዛሬ ላይ የደረሰው የመከላከያ ሠራዊት፤ ከዛሬ ባሻገር ያለው ነገ ብዙ መሥራትን የሚጠይቀው ስለመሆኑ አያሌ ማሳያዎች አሉ።ይሄም መከላከያ ሠራዊቱ ከትናንቱም ከዛሬውም የላቀ ግዳጅ እንዳለበት የሚያመላክት፤ ግዳጁን የሚመጥን ሁሉን አቀፍ ዝግጁነት እንደሚሻው የሚጠቁም፤ ከዘመኑ ጋር የሚዘምን ማንነት እንዲኖረውም የሚያስገድድ ነው፡፡

በዚህ ረገድ ትናንት የመከላከያ ሠራዊት ቀን በተከበረበት ወቅት የተላለፉ መልዕክቶች፣ የታዩ ትርኢቶች፣ አጠቃላይ የሁነቱ ድባብ ሠራዊቱ ከትናንቱም ሆነ ከዛሬው ይልቅ ስለ ነገው መንገዱና ግዳጁ በእጅጉ ትኩረት መስጠቱን መመልከትም፣ መረዳትም ይቻላል።የሠራዊቱ ሰብዕናና ሥነልቡና፣ የሰው ኃይሉ ብቃት፣ የቴክኖሎጂው ግብዓት፣ የትጥቅ አቅሙና ሌሎችም ዘርፈ ብዙ ለጦር ኃይል አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ሁሉ በጊዜውና በዘመኑ ተለክተው የተደራጁ ናቸው፡፡

ይሄ ደግሞ ሠራዊቱ እንደ ሀገር የሀገርና ሕዝብን ደህንነትና ሉዓላዊነት የማስጠበቅ፤ እንደ ዓለምም ዓለምአቀፋዊ የሠላም ማስከበር ግዳጅን ለመወጣት የሚያስችል ምሉዕነት እንዳለው ያረጋገጠ ሆኗል።በሁነቱ ሀገር ባላት አቅም እንድትኮራ፤ ሕዝብም በተፈጠረለት አስተማማኝ ደጀን  እንዲመካ ያስቻለም ነው።በውስጥ ባንዳዎች፤ በውጭም በኢትዮጵያ ላይ መልካም ነገርን የማይሹ ኃይሎች ቆም ብለው እንዲያስቡ ብቻ ሳይሆን እጃቸውን እንዲሰበስቡ፤ ወደ ቀልባቸው እንዲመለሱ የሚያስገድድ ትዕይንትም ነበር፡፡

ይሄ ደግሞ ከ116 ዓመት የጸና መሠረት ካለው የአንድ የመከላከያ ተቋምና ሠራዊት የሚጠበቅ ነው።ምክንያቱም ይሄ የመከላከያ ተቋምና ሠራዊት ታሪኩን የሚያውቅ ከታሪኩ የተማረ፤ አባቱን የሚያከብር ከጀግኖች አባቶቹ እሴትን የወረሰ፤ ሕዝብን የሚያከብር  ብልሃትንና ብርታት የቀሰመ፤ ራሱን በልኩ የተረዳ በውስጡ ያለውን እምቅ አቅም አውጥቶ መጠቀም የቻለ፤ ነገውንም ቀድሞ በመተንበይ ስለ ነገው አስቦ ራሱን በልኩ ያዘጋጀ የሀገር መከታ፣ የሕዝብም መመኪያ ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የባህር በር ማጣት

### የሚያስከፍለው ዋጋ

**ምሕረት ሞገስ**

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በዓለምአቀፍ ደረጃ 44 ሀገራት የባህር በር የላቸውም፤ ከእነዚህ ውስጥ በቆዳ ስፋቷ ትልቅ የምትሰኘው ወደብ የሌላት ሀገር የመካከለኛዋ ኤዢያ ካዛኪስታን ናት።በቆዳ ስፋት ትንሿ ደግሞ በአውሮፓ ውስጥ ያለችው ቫቲካን ናት፤ ቫቲካን ደግሞ በቆዳ ስፋቷ ብቻ ሳይሆን የሕዝብ ቁጥሯም በዓለም በ195ኛ ደረጃ ላይ የተቀመጠች ናት።

በዓለም በሕዝብ ብዛቷ 11ኛ ላይ የተቀመጠችው እና 120 ሚሊዮን የሕዝብ ቁጥር ያላት፤ ለዘመናት የባህር በር ኖሯት የቆየችው፤ በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎች የባህር በሯ እየቀነሰ ከሦስት አስርት ዓመታት ወዲህ የባህር በር ያጣችው ደግሞ፤ አፍሪካዊቷ ሀገር  የእኛዋ ኢትዮጵያ ናት።

የተባበሩት መንግሥታት ጥናት እንደሚያሳየው፤ የአንደ ሀገር አጠቃላይ ምርት ዕድገት (ጂዲፒ) ከ25 እስከ 30 በመቶ የባህር በር ነው።ከሰሞኑ በቀይ ባህር እና በወደብ ጉዳይ ላይ ያተኮረ ማብራሪያ የሰጡት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እንደተናገሩት፤ በጥናቱ መሠረት ለምሳሌ ኢትዮጵያ ጂዲፒዋ 100 ቢሊዮን ዶላር ቢሆን፤ ዓይኗ እያየ ከ25 እስከ 30 ቢሊዮን ዶላር ታጣለች ማለት ነው።ስለዚህ ኢትዮጵያ አሁን 15 ቢሊዮንም ሆነ 20 ቢሊዮን ወይም 30 ቢሊዮን ዶላር ኢንቨስት አድርጋ የባህር በር ብታገኝ ያዋጣታል።

እንደኢትዮጵያ ወደብ አልባ የሆኑ ሀገሮች ከዋና ዋና የገበያ ማዕከሎች የተገለሉና የራቁ መሆናቸው፤ የባህር በር የሌላቸው መሆኑ ለኢኮኖሚ ዕድገታቸው ከፍተኛ ማነቆ ይሆንባቸዋል።‹‹አሰብ የማን ናት?›› በሚለው መጽሐፋቸው ያዕቆብ ኃይለማርያም (ዶ/ር) እንደገለፁት፤ ኢትዮጵያ ወደ ውጭ የምትልከውና ከውጭ የምታስገባው ጠቅላላ ንግድ ከ90 በመቶ በላይ የሚከናወነው በባህር ነው።ይህንን ለማከናወን ከ1983 ዓ.ም በፊት ኢትዮጵያን ከማስከፈል ይልቅ ገቢ የሚያስገኘው ወደብ በ2003 ዓ.ም አካባቢ በቀን ሦስት ሚሊዮን ዶላር ወጪ እያስወጣት ነበር።ይህ የክፍያ ወጪ እንጂ የሚያስገኘው ምንም ዓይነት ገቢ የለም።ኢትዮጵያ የባህር በር ባታጣና እንደቀድሞ በነፃ የራሷ ወደብ ቢኖራት፤ ገንዘቡ በየዓመቱ ሃያ እና ሰላሳ ፋብሪካ ለመገንባት እና ለብዙዎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ያስችላት ነበር ሲሉ የኢትዮጵያን ጉዳት አስረድተዋል።

ዓለምአቀፍ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት፤ በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ያሉ ሀገሮች ላይ ጥናት ሲካሔድ ወደብ ያለው ሀገር በ24 ዓመት ውስጥ ኢኮኖሚው በእጥፍ ሲያድግ፤ ወደብ የሌለው ሀገር ግን ኢኮኖሚውን በእጥፍ ለማሳደግ 34 ዓመት ይፈጅበታል።ለእዚህ ቀላሉ ማሳያ ወደብ የሌላቸው ሀገራት የወደብ የትራንስፖርት ወጪያቸው ወደብ ካላቸው ጋር ሲነፃፀር በአራት እጥፍ የሚጨምር መሆኑ ነው።

በሌላ በኩል የባህር በር አለመኖሩ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የሚፈጥረው ተፅዕኖ ሲታይ፤ የሀገር ውስጥ ምርትን ወደ ውጭ ለመላክም ሆነ፤ ጥሬ ዕቃ ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት የተለያዩ ከአምራቹ ሀገር ቁጥጥር ውጪ የሆኑ ጉዳዮችም ያጋጥማሉ።ውጣ ውረድ እና ከፍተኛ የወደብ ኪራይ ክፍያ ጉዳት ብቻ ሳይሆን የወደቡ ባለቤት ሀገር የሚሰጠው የተቀላጠፈ አገልግሎትም ወሳኝነት አለው።«አንድ ሀገር የባህር በር ከሌለው የግብርና ምርትም ሆነ ማዕድን እንዲሁም ሌሎችም ለዓለም ገበያ ሊቀርቡ የሚችሉ ምንም ዓይነት ምርቶች ቢያመርትም ምንም ዋጋ የለውም፤» የሚለው የጠቅላይ ሚኒስትሩ ንግግርም ይሄንኑ እውነታ ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው፡፡

በእርግጥም መረጃዎች እንደሚያመላክቱት፤ ምርት አምርቶ ለዓለም ገበያ ለማቅረብ ፈተናው ከበዛ ውሎ አድሯል።ለጅቡቲ ወደብ ኢትዮጵያ የምትከፍለው ታሪፍ በየጊዜው እያደገ ሲሆን፤ በአንድ ጊዜ 25 በመቶ ጭማሪ የታየበት ጊዜ መኖሩ እየተጠቆመ ነው።በውጭ ምንዛሪ የተገዛው ጥሬ ዕቃም ሆነ መድኃኒትን ጨምሮ የተለያየ ምርት ወደ ሀገር ሲገባ የባህር በር ባለመኖሩ፤ ተጨማሪ ወጪን ያስከትላሉ።በዚህ ሳቢያ ዜጎች ከፍተኛ የኑሮ ጫና ያጋጥማቸዋል።

“

**አሁን ብቻ ሳይሆን በተለይ ወደ ፊት የባህር በር ማግኘት ለኢትዮጵያ ዕድገት እና ዘላቂ ሠላም ወሳኝ ብቻ ሳይሆን የህልውናዋ ጉዳይም ነው**

የባህር በር ባለመኖሩ ሰዎች ለሚለብሱት ልብስ፣ ለሚያድሩበት መጠለያ እና ለሚመገቡት ምግብ ሳይቀር የሚያወጡት ወጪ ከፍተኛ ይሆናል።ይህንን ገንዘብ ማግኘት ካልቻሉ የመኖር ህልውናቸው አደጋ ውስጥ እስከ መግባት ይደርሳል።የዋጋ መናር ዜጎችን በእጅጉ ከማማረር በተጨማሪ የሀገር የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ ሊፈጥር የሚችለው ተፅዕኖ ከባድ ይሆናል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደተናገሩት፤ አሁን ብቻ ሳይሆን በተለይ ወደ ፊት የባህር በር ማግኘት ለኢትዮጵያ ዕድገት እና ዘላቂ ሠላም ወሳኝ ብቻ ሳይሆን የህልውናዋ ጉዳይም ነው።አሁን ላይ የወደብ ክፍያ እየተፈፀመ፤ ያለውን ሕዝብ ማኖር ችለናል።ወደ ፊት በ2030 ወደ 150 ሚሊዮን፤ በ2050 ደግሞ ቁጥሩ በእጥፍ ይጨምራል ተብሎ የሚገመት ሕዝብን ያለባህር በር እንዲኖር መፍረድ በየትኛውም መልኩ ተገቢነት የጎደለው ብቻ ሳይሆን ሊሆን የሚችልም አይደለም።

የባህር በር ማጣት ይህንን ሁሉ ጉዳት የሚያስከትል መሆኑ ያለፈውን በማስታወስ እንድንቆጭ ያስገድደናል።ያም ቢሆን ግን ሙሉ ለሙሉ እንዳለፈ ታሪክ በርን ዘግቶ ከማለቅ እና ከመፍረስ በፊት የባህር በር ሊገኝባቸው የሚችሉ ሠላማዊ አማራጮችን ማየቱ የሚያስከፋ አይደለም።ከላይ እንደተገለፀው፤ የባህር በር አለመኖሩ በቀጣይም ኢኮኖሚውን አደጋ ላይ መጣሉ አይቀርም፡፡

ይህ ሲሆን ደግሞ የሀብት ሽሚያን እና የፖለቲካዊ ቀውስ ያመጣል።ፖለቲካው መታመሙ ለተደጋጋሚ ግጭት ይጋብዛል።ይህ ደግሞ እያደገ ሲሔድ ሀገር እስከማፍረስ የዘለቀ ጉዳት ይኖረዋል።ይህ ሁሉ ሲጠቃለል የባህር በር በተለይ የሕዝብ ቁጥሯ ሰፊ ለሆነ እንደኢትዮጵያ ላለች ሀገር የኢኮኖሚ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ፖለቲካዊ ጉዳይ ከመሆን አልፎ የሀገርን ህልውና አደጋ ላይ እስከመጣል የሚደርስ አሳሳቢ አጀንዳ ነው።

በእርግጥ የዓባይን ውሃ የመጠቀም ጉዳይ ከ50 ዓመት በፊት ህልም ነበር።በብዙ ትግል እና በምክክር አሁን በዓባይ ወንዝ ላይ የዓባይ ግድብ ተገንብቶ ኃይል ማመንጨት ጀምሯል።የባህር በር የማግኘት ጉዳይም ዛሬ ሃሳቡ መነሳቱ እንደትልቅ ጉዳይ ተገልፆ የሚያስወቅስ ሊሆን ይችላል።ነገር ግን ዛሬ ሃሳቡ ከተነሳ ይህኛው ትውልድ ባይችለውም፤ ቀጣዩ ትውልድ ኢትዮጵያ የባህር በር እንዲኖራት ማድረግ የሚችልበት ሁኔታ ይፈጠራል።

**ሠላም!**

# «ኢትዮጵያ በኃይልና በወረራ ማሳካት የምትፈልገው አንዳች ነገር የለም»

**- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)**

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በኃይልና በወረራ ማሣካት የምትፈልገው አንዳች ነገር እንደሌለ ማረጋገጥ እፈልጋለሁ ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትርና የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ተናገሩ።

116ኛው የመከላከያ ሠራዊት ቀን "በተፈተነ ጊዜ ሁሉ የሚጸና የድል ሠራዊት" በሚል መሪ ሀሳብ በተለያዩ ወታደራዊ ትርዒቶች በመስቀል አደባባይ ተከብሯል።

በበዓሉ የተገኙት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ኢትዮጵያ በኃይልና በወረራ ማሣካት የምትፈልገው አንዳች ነገር እንደሌለ ለመላው ኢትዮጵያውያንና ለሀገር መከላከያ ሠራዊት ለማረጋገጥ እወዳለሁ ብለዋል።

ኢትዮጵያ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ውይይት ያስፈልጋል ስትል ወረራ ይደረጋል ብለው የሚያስቡ ሰዎች አሉ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ኢትዮጵያ ግን የትኛውም ሀገር ላይ ወረራ ፈጽማ አታውቅም፤ አሁንም አትፈጽምም ሲሉ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ በኃይልና በወረራ ሳይሆን በውይይትና በትብብር ማዕቀፍ በጋራ ለመጠቀም ትፈልጋለች ያሉት ዶክተር ዐቢይ፤ በተለያዩ ሀገራት ወንድሞቻችን ላይ የምንስበው የመሣሪያ ቃታ እንደማይኖር ላረጋግጥ እወዳለሁ ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳመለከቱት፤ የኢትዮጵያ መከላከያ እንደስሙ ሀገሩን የሚከላከል እንጂ ማንንም ተነስቶ የሚያጠቃ አይደለም።

የመከላከያ ሠራዊት ዋነኛ ዓላማ ሰላም እንዳይጠፋ መጠበቅ፣ የጠፋ ሰላምን መመለስና የተገኘውን ሰላም አጽንቶ ማቆየት ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ሠራዊቱ ደሙን የሚያፈሰውና ሕይወቱን የሚሰዋው ሰላምን ለማረጋገጥ መሆኑን ማገንዘብ ይገባል ብለዋል።

መከላከያ ሠራዊት በሀገር ውስጥም ሆነ ሰላም አስከባሪ ሆኖ በተመደበበት ሀገር ሁሉ ሁሉ አርሶ አደሩን የሚያግዝ፣ ትምህርት ቤትና የጤና ተቋማትን የሚገነባው የሰላምና የልማት ምልክት ስለሆነ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የሰላም ምልክት የሆነው ሠራዊት የልማት ምልክት ሆኖ እንዲቀጥልም የአስተሳሰብ፣ የአደረጃጀትና የማድረግ አቅሙ እንዲጎለብት ሪፎርም መካሄዱን አንስተዋል።

ባለፉት ዓመታት መከላከያ በተለይ ሀገራዊ አስተሳሰብ እንዲይዝ፣ በተለያዩ ጠንካራ አደረጃጀቶች እንዲዋቀርና በማድረግ አቅሙ ዙሪያ ዘመናዊ የጦር መሣሪያዎችን እንዲታጠቅ ሰፊ ተግባራት መከናወናቸውን አስረድተዋል።

መከላከያ አቅሙ የደረጀና ታሪክ ጠገብ ተቋም ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ሠራዊት የተደራጀው ለኢትዮጵያውያን፣ የሚመራው በኢትዮጵያውያንና የሚሠራው ለኢትዮጵያ መሆኑን ማወቅ ይገባል ብለዋል።

ስንኖር ኢትዮጵያዊ ስንሞት ኢትዮጵያ የተባለው ሀሳብ በሰፊው የሚገልጸው መከላከያን እንደሆነም ጠቁመው፤ መከላከያን ለማፍረስ የሚነሱ ኃይሎች ችግሮቻቸውን በሰላምና በውይይት በመፍታት ሀገር ማጽናት አለባቸው ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ኢትዮጵያዊነትን በተግባር ያሳየውን ተቋም ታሪክ በመጠበቅ የሠራዊቱን ቀን በየዓመቱ ጥቅምት 15 ቀን እንዲከበር ላደረጉ የመከላከያ አመራሮችና አባላትም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ምስጋና አቅርበዋል።

ታሪኩንና መሠረቱን የሚያውቅ ይወልዳል፤ ይዋረሳል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ መከላከያ ታሪኩን የሚያውቅና የሚያስከብር በመሆኑ ሊወደስ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

የመከላከያ ሠራዊት ቀን በዓል ላይ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈጉባኤ አቶ ታገሰ ጫፎ፣ የቀድሞ የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሙላቱ ተሾመ (ዶ/ር)፣ የክልል ርዕሳነ መስተዳድሮችና ሚኒስትሮች፣ የሠራዊቱ ከፍተኛ አመራሮችና የተለያዩ ሀገራት የጦር አዛዦች እንዲሁም ከተለያዩ አካባቢዎች የመጡ ኢትዮጵያውያን ተገኝተዋል።

# መከላከያ ታሪኩንና አንድነቱን ጠብቆ ...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

ሲከበር የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ እንደገለጹት፤ መከላከያ የአባቶቹን የጀግንነት ዕውነታ በመጠበቅ የሚጓዝ በመሆኑ የሠራዊቱን ቀን ታሪኩን በጠበቀ መልኩ አክብሯል።

በየዘመኑ የመጡ ገዢዎች የሠራዊት ቀንን በመለዋወጥ ታሪክ አዛብተዋል ያሉት ፊልድ ማርሻሉ፤ ወገንተኛ ትርክቶች ፈተና ውስጥ ካስገቧቸው ተቋማት አንዱ የመከላከያ ሠራዊት እንደነበር አንስተዋል።

በኢሕአዴግ ዘመን የመከላከያ በዓል የካቲት ሰባት ቀን 1987 ዓ.ም ሆኖ እንዲከበር መወሰኑ አንዱ ታሪካዊ ስህተት እንደነበር አስታውሰዋል።

ውሳኔው ለዘመናት የሀገርን ሕልውና ጠብቆ የኖረውን የሠራዊት ታሪክ የዘነጋና የጀግኖችን ውለታ ያላማከለ ታሪካዊ ስህተት እንደነበረ ጠቁመዋል።

ከለውጡ ወዲህ የተሳሳተውን ውሳኔ በማስተካከል የኢትዮጵያ ሠራዊት እንደ ተቋም የተመሠረተበት ጥቅምት 15 ቀን የሠራዊቱ ቀን ሆኖ እንዲከበር መወሰኑን ገልጸዋል።

ጥቅምት 15 ቀን 1900 ዓ.ም ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ፊታውራሪ ሃብተጊዮርጊስ ዲነግዴን የመጀመሪያው የጦር ሚኒስትር አድርገው የሾሙበትና ለሠራዊቱ መሠረት የጣሉበት ቀን በመሆኑ በየዓመቱ የመከላከያ ቀን ሆኖ መከበሩን እንደሚቀጥል አመላክተዋል።

የሠራዊቱ አመራሮችና አባላት ከቀደምት ጀግኖቻችን በክብር የተረከብናትን ሀገር አስጠብቀን ለመጪው ትውልድ ለማስተላለፍ ቃል እንገባለን ያሉት ፊልድ


ፎቶ፡ እዮብ ተፈሪ
ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ

ማርሻሉ፤ ሠራዊታችን ከውጭና ከውስጥ የሚሰነዘሩ ጥቃቶችን ለመመከት ዝግጁ ነው ብለዋል።

በአሁኑ ወቅት የውጭ ጠላቶች ኢትዮጵያን በቀጥታ ሊያሸንፉን እንደማይችሉ ስለተረዱ ያኮረፉ የመሰሏቸውን ወገኖች በተለያየ መንገድ በመደገፍ ሠራዊቱን አላስፈላጊ መስዋዕትንት እያስከፈሉ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በእልህ፣ በመጠላላትና በኃይል ሀገር ማፈራረስ እንጂ ጥቅም እንደማይገኝ ማወቅ እንደሚገባ ተናግረው፤ ከሱዳን፣ ሊቢያና ከሌሎች ሀገራት ስህተት መማር እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

የመከላከያ ሚኒስትር አብርሃም በላይ (ዶ/ር) በበኩላቸው የመከላከያ ሠራዊት ቀን አስመልክቶ ባስተላለፉት መልዕክት፤ ከ116 ዓመት በፊት በአህጉር ብሎም በዓለም አቀፍ ደረጃ ቀደምት ከሆኑት የጦር ሠራዊቶች ተርታ የሚመደበውና የኢትዮጵያ አለኝታና ተስፋ የሆነው መከላከያ የጦር ሚኒስቴር በሚል መጠሪያ ስም መቋቋሙን አስታውሰዋል።

ከታሪኩ በመነሳት ሲከበር የቆየውን የመከላከያ ቀን አከባበር በመከለስና፣ ተገቢውን ማስተካከያ በማድረግ ከ2015 ዓ.ም ጀምሮ እንደ አዲስ እየተከበረ መሆኑን ገልጸዋል።

እውነተኛና ጠንካራ ትርጉም ያለውን ተቋማዊ ታሪክ በመዘከር ቀኑ ማክበር መቻሉ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያንን በሙሉ ያስደሰተና ለሠራዊታችን የሚሰጠውን የላቀ ክብርና ምስጋና በድጋሚ ያረጋገጠ ነው ብለዋል።

116ኛው የመከላከያ ሠራዊት ቀን በተለያዩ ከተሞችና የኢትዮጵያ ሰላም አስከባሪ በሚገኝባቸው ጎረቤት ሀገራት ተከብሯል።

# «ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ መድረኮች ...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

አቀፋዊ፣ አህጉራዊና ቀጣናዊ ስምምነቶች፣ መርሆዎችና ማዕቀፎች በተጨማሪ በራሷ የስደተኞች ፖሊሲ የምትመራ አገር መሆኗን ተናግረዋል።

ስደተኞች ኢትዮጵያን እንደ አገራቸው እንዲያዩ በማድረግ ረገድም ትልቅ ሥራ መሠራቱን አንስተዋል።

እ.ኤ.አ በ2019 የገባችውን ቃል ኪዳን በመፈጸም ለስደተኞች የሚመች ድባብን በመፍጠር ረገድ እያከናወነች ያለውን ተግባር በማጠናከር በቀጣይ የ2023 ጉባኤ ላይ ያፀደቀቻቸውን ስድስት ቃል ኪዳኖች እንደምታቀርብ አስታውቀዋል።

የስደትና ተመላሾች አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ጠይባ ሐሰን፤ ኢትዮጵያ ከጎረቤት ደቡብ ሱዳን፤ ሶማሊያ፣ ሱዳን እና ኤርትራ እንዲሁም የመንና ሶሪያን ጨምሮ ከ26 ሀገራት ለመጡ አንድ ሚሊዮን ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች ከለላና ጥበቃ በማድረግ ላይ ትገኛለች ብለዋል።

እ.ኤ.አ ታህሳስ 2023 በስዊርላንድ ጄኔቫ በሚካሄደው ዓለም አቀፍ የስደተኞች ጉባኤ (Global Refugee Forum) የሚቀርቡ ስድስት ቃልኪዳኖች በትናንትናው ዕለት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን፣ ዘርፉ የሚመለከታቸው ሚኒስትሮችና የፌዴራል መንግሥት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች በተገኙበት ውይይት ተደርጎባቸው ጸድቀዋል።

ቃል ኪዳኖቹ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ ምላሽ፣ የተመረጡ የስደተኛ መጠለያ ጣቢያዎችን ወደ ከተማነት ማሳደግ፣ በስደተኞች አካባቢዎች የግሉን ዘርፍ የኢንቨስትመንት ተሳትፎ ማሳደግ፣ የበይነ መረብ ተደራሽነትን ጨምሮ የስደተኞችንና ተቀባይ ኅብረተሰብን በምግብ ራስን ለማስቻልና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ የመሬትና መስኖ ተጠቃሚነትን ማስፋት መሆናቸው በመድረኩ ተጠቅሷል።

ወደ ትግበራ ሲገባ፣ ቃል ኪዳኖቹ የስደተኞችና ተቀባይ ማኅበረሰቦችን ሕይወት ለማሻሻል ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንደሚኖራቸውም ተሳታፊዎች ተናግረዋል።

ለተግባራዊነታቸውም የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ኤጀንሲ የባለድርሻ አካላትና አጋሮች ብሎም የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ቅንጅት ድጋፍና ርብርብ አስፈላጊ መሆኑም ነው የተገለጸው።


አቶ ኃይሉ አዱኛ

# ከኦሮሚያ የተፈናቀሉ ዜጎች መልሶ የማቋቋም እንቅስቃሴ ተጀምሯል

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል በፀጥታ ችግር ምክንያት ከቀዬአቸው የተፈናቀሉ ዜጎች መልሶ ለማቋቋም ኦሮሚያና አማራ የጋራ እንቅስቃሴ መጀመራቸው የኦሮሚያ ክልል ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ አስታወቀ።

የኮሙዩኒኬሽን ቢሮ ኃላፊው አቶ ኃይሉ አዱኛ የሁለቱ ክልሎች ባለሥልጣናት ሰሞኑን በኦሮሚያ ክልል የተፈናቀሉ ዜጎች መልሶ ለማቋቋም በባሕርዳር ከተማ ያደረጉት የጋራ መድረክ አስመልክተው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ መልሶ የማቋቋም ሥራ የሚያከናውኑ የጋራ ኮሚቴ ለማቋቋም ተስማምተዋል።

እንደ አቶ ኃይሉ ማብራሪያ፣ የጋራ ኮሚቴው ቀዳሚ ተግባር ተፈናቃዮቹ ከየት ወረዳና ቀበሌ እንዲሁም መቼ እንደተፈናቀሉ ተገቢውን መረጃ መሰብሰብና ማጣራት ነው። የተፈናቃዮቹ የሥራ ሁኔታ ማለትም አርሶ አደር ከሆነ የመሬት ይዞታና የአፈር ግብር ማስረጃ እንዲሁም የቤተሰብ ብዛት በውል አጣርቶ መረጃ ያቀርባል። በመቀጠልም የተለያዩ ሥራዎችን የሚከውኑ ከሥሩ ንዑሳን ኮሚቴዎችን ያዋቅራል።

የኦሮሞና የአማራ ሕዝብ ለዘመናት አብሮ የኖረ፣ በጋብቻ የተጋመደና በደም የተሳሰረ ሕዝብ ነው ያሉት አቶ ኃይሉ፤ ሆኖም ግን በፖለቲካ ቁማርተኞች በፍቅርና በመከባበር አብረው እየኖረ ያሉ ሕዝብ ከቀዬው እንዲፈናቀልና በጥርጣሬ ዓይን እንዲተያይ ምክንያት ሆነዋል ብለዋል። አለፍ ብሎም አንዳንድ የፖለቲካ ነጋዴዎች ችግሩ ለፖለቲካ ፍጆታ እንዲሆንላቸው ዜጎች ወደ ቀዬአቸው እንዳይመለሱ ከፍተኛ ቅስቀሳ እያደረጉ መሆናቸውንም አውስተዋል።

አቶ ኃይሉ፣ ከኦሮሚያ ተፈናቅለው ወደ አማራ ክልል ተሰድደው ችግር ላይ ላሉት ዜጎች አሸባሪው ሸኔ ተጠያቂ ሲያደርጉ በኦሮሚያ በተለይ ከሆሮ ጉዱሩ ወለጋ ተፈናቅለው ችግር ላይ ላሉት ዜጎች ደግሞ ጽንፈኛ የፋኖ ቡድን ተጠያቂ አድርገዋል። የቡድኖቹ እኩይ ዓላማ ለማክሸፍ ሁለቱም ክልሎች በተለየ መልኩ በጋራ ለመሥራት ቁርጠኝነትም አቅምም እንዳላቸው አስገንዝበዋል።

መልሶ የማቋቋም ሥራው በርካታ ሀብት የሚጠይቅ በመሆኑ በአንድ ጀምበር የሚከናወን እንዳልሆነ ገልጸው፤ ነገር ግን የተጣራውን መረጃ መሠረት በማድረግ የፀጥታ ሁኔታቸው አስተማማኝ በሆኑ አካባቢዎች ላይ መልሶ የማቋቋም ሥራ በቅርቡ እንደሚጀመር አመልክተዋል። በተመሳሳይ መልኩ የፀጥታ ችግር ባለባቸው አካባቢዎች ነፃ ለማድረግና መልሶ የማቋቋም ሥራው ቀጣይነት እንዲኖረው በፀረ ሰላም ኃይሎች ላይ የተቀናጀ ሥራ ይሠራል ብለዋል።

በክልሉ የተፈናቀሉ ዜጎች መልሶ የማቋቋም ሥራው በዋናነት የክልሉ መንግሥትና የክልሉ ሕዝብ ኃላፊነት ነው ያሉት አቶ ኃይሉ፤ ሥራው በርካታ ሀብትና ትብብር የሚፈልግ ጉዳይ እንደመሆኑ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም ዓለም አቀፍ ድርጅቶችን በሂደቱ ተባባሪ ለማድረግ በትኩረት እንደሚሠራ አስታውቀዋል።

ማህበራዊ

# ሀገርኛ

# ቦር- የፈውስ ተራራ





የየም ብሔረሰብ አባላት በየዓመቱ ጥቅምት 17 «በቦር ተራራ» ላይ ለመድኃኒት ለቀማ ይሰማራሉ

**ዳግም ከበደ**

ኢትዮጵያ የባህል፣ የታሪክ፣ የተፈጥሮና የቅርስ ሀብቶች በስፋት ከሚገኙባቸው ቀዳሚ ሀገራት ተርታ ትመደባለች። ይሁን እንጂ እነዚህን ሀብቶች በሚፈለገው መጠን የማስተዋወቅ፣ የማልማትና ከሀብቱ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ አቅም አሁንም ድረስ እንዳልጎለበተ ይታመናል። ሀገሪቱ ለዓለም በኪነ ጥበብ፣ ባህልና ባህላዊ ሕክምና፣ በተፈጥሮ፣ በኪነ ሕንፃና ሥነ ጽሑፍ እውቀት ያበረከተች መሆኗም እሙን ነው። ለዚህ እንደ ጥሩ ማሳያ የሚሆኑት ቀደም ያሉ የሥልጣኔ ዐሻራዎች ናቸው።

አሁን ላይ በዓለም የማይዳሰሱና የሚዳሰሱ ቅርስነት ተመዝግበው የሚገኙ ኪነ ሕንፃዎች፣ የሥነ ጽሑፍ ውጤቶች፣ ባህላዊ እሴቶች እንዲሁም ታሪካዊ ክስተቶች ሀገራችን ለመላው የሰው ልጆች ዛሬ ላይ የመድረስ ምክንያት እንደነበረች ህያው ምስክር ናቸው።

በተለይ በቀደምት ሥነ ጽሑፍ ውስጥ ከሕክምና ጥበብ ጋር ተያይዞ ቀደምት ኢትዮጵያውያን ያስቀመጧቸው የምርምር ውጤቶችና ግኝቶች በብዙኃን ዘንድ በእግር በፈረስ የሚፈለጉ ናቸው። ታላላቅ ሀገራት በብራና መጽሐፍት ላይ የተከተቡ ጥበቦችን ለመረዳት የግዕዝ ቋንቋን ጭምር በከፍተኛ የትምህርት ተቋሞቻቸው እንደ አንድ ዘርፍ ትኩረት ሰጥቶ እስከመሥራት ደርሰዋል።

በሀገራችን ከቀደምት ጥበቦች እንዲሁም ከሀገር በቀል እውቀቶች መካከል የባህል ሕክምና ከፍተኛ ትኩረት እንደተነፈገው ብዙዎች ሲናገሩ ይደመጣል፡፡ የባህል ሕክምና ጥበብ ከሁሉም የዓለም ሀገሮች በፊት የተጀመረና ዓለም ሰልጥኖ ዘመናዊ ሕክምና ከመጀመሩ በፊት በዘርፉ የተሰማሩ ጠበብት አባቶቻችን እና እናቶቻችን ሁሉንም ዓይነት በሽታ የሚፈውሱበት መድኃኒት እንደነበራቸው ይገለጻል፡፡ መድኃኒቶቹንም ከተለያዩ ዕጽዋት በመመራመርና በመቀመም ለታማሚው መጥኖ በመስጠት በሀገሪቱ በሰፊው ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጉ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ይመሰክራሉ።

እንደ አለመታደል ሆኖ ዓለም በሕክምናው ዘርፍ ዛሬ የደረሰበት ደረጃ ላይ ቢደርስም በእኛ ዘንድ ግን የውጭውን ሥልጣኔ ተመልካች በመሆናችን ሀገር በቀል የሆነውን ባህላዊ እውቀት በአግባቡ ባለመረከባችን ቀደምት የሆነው የባህል ሕክምና ተንቆና ተረስቶ እንዲኖር ተፈርዶታል፡፡

ይህ እውቀት ወደ ዘመናዊው የሕክምና ሥርዓት አይግባ እንጂ ዛሬም ድረስ በማኅበረሰቡ ውስጥ የፈውስ መንገድና ዘዴ ተደርጎ ይወሰዳል። ጅምርና ያልጎለበተ ቢሆንም ባህላዊ የሕክምና ዘዴዎችን ከዘመናዊው ጥበብ ጋር አስተሳስሮ ለማስኬድ ምርምር የሚያደርጉ ውስን ተቋማት አሉ። ከሁሉ በላይ ግን የቀደመውን ባህላዊ ሥርዓትና እሴት ጠብቆ በማቆየት ረገድ ማኅበረሰቡ የማይተካ ድርሻውን እየተወጣ ይገኛል። ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ የ «የም» ማኅበረሰብ ተጠቃሽ ነው።

## የም- ባህላዊ እሴቶች የመጠበቅ ምሳሌ

ከላይ ለማንሳት እንደሞከርነው የየም ማኅበረሰብ ባህላዊ እሴቶችን እና ጠቃሚ ልማዶችን ከትውልድ ወደ ትውልድ ጠብቆ በማስተላለፍ ከሚታወቁት መካከል አንዱ ነው። መረጃዎች እንደሚያመለክቱት «የም» የሚለው ስያሜ የብሔረሰቡ መጠሪያ ሲሆን «የምሳ» ደግሞ የብሔረሰቡ መደበኛ ቋንቋ ነው። ብሔረሰቡ ከአስራ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ታዋቂና ጠንካራ መንግሥት መስርቶ ይኖር እንደነበርም የጥናት መዛግብት ያስረዳሉ። የየም ብሔረሰብ አሰፋፈሩን በኮረብታማና ወጣ ገባ መልከዓ ምድር ላይ ያደረገ ነው። ከጊቤ ወንዝ አንስቶ እስከ ቦር ተራራ ያለው አቀማመጥም ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ የሚሄድ በመሆኑ ለመኖሪያነት አመቺ መሆኑን ነዋሪዎች ይናገራሉ።

ከመዛግብትና ከዞኑ ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ባለሙያዎች መረዳት እንደተቻለው፤ ብሔረሰቡ የሰፈረበት አካባቢ የአየር ንብረት ደጋና ወይናደጋ ሲሆን፣ ምሥራቃዊው ክፍልና የጊቤ ተፋሰስ በቆላነት ይመደባል።

ብሔረሰቡ የራሱ የሆነ ባህል፤ ቋንቋ፤ ታሪክና ወግ አለው። በአካባቢው ታሪካዊ ቤተ መንግሥት፣ የእምነት ስፍራዎች፣ ዕድሜ ጠገብ ደኖች፣ ትክል ድንጋዮች፣ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ዋሻዎች በብዛት ይገኛሉ። በርካታ ትክል ድንጋዮች የሚገኙበት ስፍራ «ዞፍካር» ይባላል። ይህ ስፍራ የየም የመጨረሻ ንጉሥ በነበረው አባቦግቦ ዘመን ቀብር ይፈፀምበት ነበር፡፡ አካባቢው በታሪካዊነቱና በአንጋፋነቱ ከሌሎች የተመረጠ በመሆኑም በፓርክ ክልልነት እንዲለይ ተደርጓል። «አንጋሪ» የተባለው ጥንታዊ ቤተ መንግሥትም በጥቅጥቅ ደኖችና በሀገር በቀል ዛፎች የተከበበ በመሆኑ በመስህብነት ያገለግላል።

የየም ብሔረሰብ የቤት ውስጥ መገልገያዎች፣ የንጉሣውያን አልባሳት፣ ከዝሆን ጥርስ የተሠሩ የትንፋሽ ሙዚቃ መሣሪያዎችና የሸክላ ውጤቶች ዕድሜ ጠገብ ከመሆናቸውም በላይ የብሔረሰቡ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች ናቸው፡፡ በብሔረሰቡ በዋንኛ ምግብነት ከአስር የማያንሱ ምግቦች ከእንሰት ውጤቶች ይዘጋጃሉ። በልዩ ማኅበራዊ ግንኙነት ወቅት የሚዘጋጅ የቆጮ ድፎ «ኮባና» ይባላል። በገንፎና በቂጣ መልክ የሚዘጋጀው ቡላም «ኬዳኦ» የሚል መጠሪያ አለው። የቆጮ ገንፎ «ናቱ» ሲባል ከጎመንና ከቆጮ የሚዘጋጀው ፍርፍር ደግሞ «ዎቶ» ይሰኛል። «ፈጨ» የሚባለውም ለሕፃናት ምግብነት የሚዘጋጅ ነው።

ከብሔረሰቡ ባህላዊ መጠጦች ዋናው «ቦርዴ ማኡሻ» ይባላል። የሚዘጋጀውም ከገብስ፣ ከዳጉሳ፣ ከቀይ ጤፍና ከብቅል ነው። ሌላው ባህላዊ መጠጥ ደግሞ «ኪአ» የሚል መጠሪያ አለው። ይህ የመጠጥ ዓይነት ውሃ ሳይጨመርበት ድፍድፉ ብቻ ተጨምቆ የሚቀርብ በመሆኑ በተጠቃሚዎች ዘንድ ተወዳጅ መሆኑ ይነገርለታል። በልዩ ዝግጅት ወቅት የሚዘጋጀው ባህላዊ መጠጥም «ኡሻ» ይባላል።

የዝግጅት ክፍላችን በዛሬው «ሀገርኛ» አምዱ ላይ በስፋት ለመዳሰስ የወደደው የየም ማኅበረሰብ ባህላዊ እሴት የሆነው ደግሞ ጥቅምት 17 በየዓመቱ «በቦር ተራራ» ላይ የሚደረገው የባህላዊ መድኃኒት ለቀማ አንዱ ነው።

## ቦር- ዓመታዊ የመድኃኒት ለቀማ

አቶ በረከት ይገዙ ይባላል። በየም ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ የቱሪስት መስህብ ጥናት ልማት ግብይት ዳይሬክተር ነው። የየም ማኅበረሰብ ከጥንት ጀምሮ ባህላዊና ታሪካዊ ሀብቶቹን ጠብቆ የማቆየትና ለትውልድ የማስተላለፍ እሴት እንዳለው ይናገራል። ከዚህ ውስጥ አንዱና ማኅበረሰቡ በስፋት የሚታወቅበት ጥንታዊ ሀብት «ባህላዊ ሕክምና» እንዲሁም የመድኃኒት ቅመማ መሆኑን በመግለፅ የሕክምና መድኃኒቱ አዘገጃጀት፣ አመታዊ የእፅዋት ለቀማ፣ የተፈጥሮ ጥበቃ እሴቶችን ያብራራል።

አቶ በረከት እንደሚለው፤ በየም ብሔረሰብ ከጥንት ጀምሮ ማኅበረሰቡ ለሕክምና አገልግሎት የሚውል ባህላዊ መድኃኒትና ቅመማን ይጠቀማል። ይህንን መድኃኒት ለሰው ልጅ ብቻ ሳይሆን የቤት እንስሳት ለሚያጋጥማቸው ህመም ፈውስ እንዲሆን ጭምር ነው። ከብቶች፣ በጎች እንዲሁም ልዩ ልዩ የቤት እንስሳት ሲታመሙ ጥቅምት 17 በዓመት አንድ ጊዜ ከቦር ተራራ የተለቀመው ባህላዊ መድኃኒት ተቀምሞ ጥቅም ላይ ይውላል ይህ ሥርዓት ከጥንት የነበረና ለትውልድ ሲተላለፍ የቆየ እሴት ነው።

በየም ጥቅምት 17 ታዋቂ በሆነው በዞኑ በሚገኝ «ቦር ተራራ» መድኃኒት ለቀማ ይወጣል። ከዚህ ቀን ውጪ በስፍራው ዓመቱን ሙሉ ምንም ዓይነት ለመድኃኒት ቅመማ የሚውል እፅዋት አይለቀምም። በዚህ ቀን አባቶች እና እናቶች ከፊት ሲሆኑ ወጣቶችና ልጆች እነርሱን ተከትለው ከኋላ እፅዋቶቹን ይለቅማሉ። ይህ የሚሆነው እውቀትና ጥበብ ከቀደምት አያቶቻቸው የተማሩት አባትና እናቶች በተመሳሳይ እውቀቱን ለማሸጋገር እንዲችሉ ልጆቻቸውን አስከትለው ትምህርቱን እንዲቀስሙ ያደርጋሉ።

በየም ዞነ ጥቅምት 17 ልዩ በዓል ነው። ከመድኃኒት ለቀማ ቀንነቱ ባሻገር ማኅበረሰቡ እርስ በእርስ መልካም ምኞቱን ለመገላለፅና ትስስሩን ለማጠናከር ይጠቀምበታል። በዚህ ምክንያት «እንኳን አደረሳችሁ፤ አደረሰን» የሚል መልዕክት ይለዋወጡበታል። የዞኑ አስተዳደር የባህል መሪዎች፣ አባቶች እናቶችና ሁሉም ማኅበረሰብ ቀኑን ልክ እንደ በዓል ቀን በመቁጠር በልዩ ድምቀት ያከብሩታል።

ጥቅምት 17 ከቦር ተራራ ላይ የሚለቀሙ ለባህላዊ መድኃኒት ቅመማ የሚያገለግሉ እፅዋት አባቶች እንደ «እርሾ» የሚጠቀሙባቸው ናቸው። ይህም ማለት የባህላዊ መድኃኒት ቀማሚዎቹ ከሌላ አካባቢ፣ ከቤታቸው ጓሮና ከልዩ ልዩ ስፍራዎች የሚሰበስቡትን ግብዓት ጥቅምት 17 ከተለቀመው ጋር በማዋሃድ ልዩና ፈዋሽ ባህላዊ መድኃኒት ያዘጋጁበታል።

ከቦር ተራራ ላይ ጥቅምት 17 እፅዋት ለቀማ የሚደረግበት ዋንኛ ምክንያት የክረምቱ ጊዜ ወጥቶ የበጋው ወራት የሚጀምርበት በመሆኑ ምክንያት ነው። በተለይ በቦር ተራራ ላይ የሚደረገው የባህላዊ መድኃኒት ለቀማ ጠዋት ፀሐይ ስትወጣ የሚደረግ ነው። ተራራው ከፍታ ላይ ያለ በመሆኑና የመጀመሪያዋ ፀሐይም በዚያ ስፍራ ላይ ስለምትወጣ የመድኃኒቱን ፈዋሽነት እንደሚጨምር አባቶች ያምናሉ። ይህንን የአባቶች እምነትና የባህላዊ መድኃኒት ቅመማ ሥርዓት ለማጥናትም የጅማ ዩኒቨርሲቲን ጨምሮ በርካታ ምሁራን ምርምር እያደረጉበት ይገኛሉ።

የየም አባቶች በቦር ተራራ እፅዋት ለቅመው የሚቀምሙት ባህላዊ መድኃኒት ለልዩ ልዩ ሕክምና አገልግሎት ይውላል። ከእጽዋቱ ከ100 በላይ ለሚሆኑ የበሽታ ዓይነቶች «ፈዋሽ» እንደሆኑ የሚታመንባቸው ባህላዊ መድኃኒቶች ይቀመማሉ።

ጥቅምት 17 በአባቶችና እናቶች እፅዋቱ ከተለቀመ በኋላ ወደ ቤት ይወሰዳል። የተሰበሰበው እፅዋትም የሚፈለገው ስፍራ እንደደረሰ በፀሐይ ብርሃን እንዲደርቅና ንፅህናው በተጠበቀ ቦታ እንዲቀመጥ ይደረጋል። ማንኛውም / ታማሚ ወደ ባህላዊ ሀኪሞቹ በመሄድ በሽታውን ሲያስረዳ እፅዋቱ እየተለየና እየተቀመመ ይሰጣል። በዚህ መንገድ የየም አባቶች የሕክምና ሥርዓቱን ዳግም ጥቅምት 17 መጥቶ ለቀማ እስኪያደርጉ ድረስ ይቀጥላሉ። የየም ማኅበረሰብ በእፅዋት ለቀማው ላይ በጋራ ይሳተፍ እንጂ መድኃኒት ቅመማውን የሚያደርጉት ግን እውቀቱና ጥበቡ ያላቸው ባህላዊ ሐኪሞች ናቸው።

የየም ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ይህንን ባህላዊ እውቀት ለማስጠናት እንዲሁም ከዘመናዊው የሕክምና ዘዴ ጋር በማስተሳሰር ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ ሥራዎችን እየሠራ ነው። ከዚህ ባሻገር ጥቅምት 17 በቦር ተራራ ላይ የሚደረገው የለቀማ ሥርዓት በቀሪው የኢትዮጵያ ክፍልና በሌሎች ዓለማችን ላይ ባሉ ጎብኚዎች እንዲታወቅና እሴቱ ተጠብቆ እንዲቆይ በመሥራት ላይም ይገኛል። ሌላው መምሪያው ይህ እሴት በምርምርና ሳይንሳዊ ዘዴ እንዲዳብር ለማድረግ የማዕከል ግንባታም እያካሄደ ነው። በማዕከሉ ምርምር ከማድረግ ባሻገርም ሕክምና እውቀቱ ባላቸው አባቶች እንዲሰጥ ለማድረግ እየተሠራ ነው። ሀገር በቀል እውቀቱን በሀገር ውስጥ ያሉም ሆነ ከሌሎች የዓለም ክፍሎች የሚመጡ ጎብኚዎች እንዲያውቁት በማድረግ አገልግሎቱን እንዲጠቀሙ እየተሠራ ነው። ይህ ማዕከል በነገው ዕለት ጥቅምት 17 ተመርቆ ሥራ ይጀምራል።

የየም ማኅበረሰብ ባህላዊ መድኃኒት በሚለቀምበት በቦር ተራራና በአካባቢው የሚገኘውን ሥነምህዳር የመጠበቅ ኃላፊነት ተጥሎበታል። ይህ ባህላዊ የመድኃኒት ለቀማ ሥርዓት ለሥነ ምህዳርና ለአካባቢ ጥበቃ የራሱን ድርሻ ይጫወታል። ማንም ሰው ከጥቅምት 17 ውጪ በዚህ ተራራ ላይ መድኃኒት መልቀምም፣ ደኑንና ልዩ ልዩ እፅዋትን መቁረጥም አይችልም። ይህ ሥርዓት መኖሩ ደግሞ አካባቢው እንዲጠበቅና ለም ሆኖ እንዲቆይ የራሱን ድርሻ ይጫወታል።

ከባህር ወለል/ ሲ ሌብል/ ሁለት ሺህ 939 ከፍታ ያለው የቦር ተራራ በየም ዞን የሚገኙ አራት ቀበሌዎች ያዋስኑታል። በእነዚህ አካባቢዎች የሚኖር የማኅበረሰቡ ክፍል የደን ሽፋኑን እና የእፅዋት ስብጥሩን የሚያዛቡ ማንኛቸውንም ዓይነት ሕገወጥ ድርጊቶች እንዳይካሄዱ የመጠበቅ ኃላፊነት ይወስዳሉ። በብሔረሰቡ ዘንድ ለበሽታ ፍቱን መድኃኒትነት ያላቸው እፅዋት የሚገኙበት ይህ ስፍራ በዚህ መልኩ ከንክኪና ሕገወጥ ድርጊት ይጠበቃል።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

# "ትምህርት ትጋትና ጥናት ይጠይቃል"

- ተማሪ ሙሉነህ እንየው

ክብረአብ በላቸው

በፈተና ስርቆት እና በኩረጃ ለበርካታ ዓመታት ችግር ሲገጥመው የነበረው የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ብሔራዊ ፈተናን ተዓማኒነት ለመጠበቅ ከ 2014 ዓ.ም ጀምሮ በአገሪቱ ባሉ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ በከፍተኛ ቁጥጥር ስር ሆኖ እንዲሰጥ ሆኗል።

በ2015 ዓ.ም የ 12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተናን 356 ሺ. 878 የተፈጥሮ ሳይንስ እና 488 ሺ. 221 የማህበራዊ ሳይንስ በአጠቃላይ 845 ሺ.188 ተማሪዎች መውሰዳቸው ይታወቃል። ከ 356 ሺ. 878 የተፈጥሮ ሳይንስ ተፈታኞች 22 ሺ. 974 ተማሪዎች የማለፊያ ውጤት አምጥተዋል። ከ 488 ሺ. 221 የማህበራዊ ሳይንስ ተፈታኞች መካከል የማለፊያ ውጤት ያመጡት 8 ሺ. 250 ብቻ መሆናቸው ተገልጿል፤ ከዚህ በተጨማሪም የትምህርት ሚኒስቴር በ 2015 ትምህርት ዘመን የ 12ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ብሔራዊ ፈተና ከወሰዱ 845 ሺ. 188 ተማሪዎች ውስጥ 27 ሺህ ተማሪዎች ከ50 በመቶ በላይ በማምጣት የማለፍያ ውጤት ማስመዝገባቸውን አስታውቋል።

ፈተናውን ከወሰዱት ውስጥ 3 ነጥብ 2 በመቶ ተማሪዎች ብቻ ማለፋቸውን የገለፀው ሚኒስትሩ ይህም ውጤት ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር በ 0 ነጥብ 01 መቀነሱንም አብራርቷል። ዘንድሮ 3 ሺ. 106 ትምህርት ቤቶች ፈተና ያስፈተኑ ሲሆን፣ ከእነዚህ ትምህርት ቤቶች ውስጥ 1 ሺ. 328 ትምህርት ቤቶች ደግሞ አንድም ተማሪ ማሳለፍ አለመቻለቸውንም አክሏል፤ በማታው የትምህርት ክፍለ ጊዜ ተምረው ፈተናውን ከወሰዱ 16 ሺ. 451 ተማሪዎች መካከልም ከ50 በመቶ በላይ ውጤት ያስመዘገቡት 12ቱ ብቻ ሲሆኑ፣ ይህም በመቶኛ ሲሰላ 0 ነጥብ 1 ነው።

ይፋ በተደረገው ውጤት መሠረት በተፈጥሮ ሳይንስ ዘርፍ 649 ነጥብ ከፍተኛ ውጤት ሆኖ የተመዘገበ ሲሆን፣ በማኅበራዊ ሳይንስ ዘርፍ ደግሞ ከፍተኛው ነጥብ 533 መሆኑ ተገልጿል፤ ይህም በአማራ ክልል ሐዲስ ዓለማየሁ ትምህርት ቤት ነው። ለፈተና ያቀረቧቸውን ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ ካሳለፉ ጥቂት ትምህርት ቤቶች አንዱ የሆነው የዚህ ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤት ተማሪ የሆነው ተማሪ ሙሉነህ እንየው የዚህ ከፍተኛ ውጤት ባለቤት ነው።

በምዕራብ ጎጃም በምትገኝና ሰከላ በምትባል አነስተኛ የገጠር ከተማ የተወለደው ተማሪ ሙሉነህ፣ ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጋር በነበረው ቆይታ እንደተናገረው፤ ከመጀመሪያው የትምህርት ደረጃዎች ጀምሮ በትምህርቱ ጥሩ ውጤት ካላቸውና ጎበዝ ከሚባሉ ተማሪዎች መካከል እንደነበር ገልፆ፤ በዘንድሮው ብሔራዊ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ጥሩ ውጤት ለማምጣት ሙሉ ጊዜውንና ሰዓቱን ትምህርቱ ላይ ብቻ በማድረግ ዝግጅት ሲያደርግ እንደቆየ ይናገራል።

ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል አዲስ ዓለም በተሰኘ ትምህርት ቤት ሰባትና ስምንተኛ ክፍልን ደግሞ ሱርበ በተባለ ትምህርት ቤት ተከታትሏል፤ ተማሪ ሙሉነህ እንደሚናገረው፤ ከእርሱ አንድ ዓመት ቀደም ብለው ካሉ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ጥሩ ውጤት ያመጡ ልጆች በውድድር ተመርጠው ወሎ አዳሪ ትምህርት ቤት መግባታቸውን ተከትሎ ይህ ዕድል እርሱንም የሚጠብቀው መሆኑን በመገንዘብ ጠንክሮ በመማር በስምንተኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና 91 ከመቶ በማምጣት ከእርሱ ቀደም እንደነበሩት ጓደኞቹ እስከ ወሎ ድረስ መሄድ ሳይጠበቅበት በደብረማርቆስ ከተማ በተከፈተው የሐዲስ ዓለማየሁ አዳሪ ትምህርት ቤት ገብቶ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ለመከታተል ችሏል።

ለ 12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ቅድመ ዝግጅት ማድረግ የጀመረው የ11ኛ ክፍል ተማሪ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ እንደሆነ የሚናገረው ሙሉነህ፤ የአራት ዓመት የትምህርት ቆይታ የሚለካበት እንደመሆኑ በዚህ ውጤታማ ሆኖ ወደሚቀጥለው ደረጃ መሸጋገር የግድ ስለሆነም የተለያየ የአጠናን ዘዴዎችን ተጠቅሞ ፍሬያማ መሆን እንደቻለ ይናገራል።

ሙሉነህ እንደሚናገረው፤ ከጓደኞቹ ጋር በቡድን ማጥናት ያዘወትር ነበር ፤ ይህም አንዱ ከሌላው ዕውቀት እየቀሰመ ማጥናቱ በግል ከሚያደርገው ዝግጅት



ባልተናነሰ ሁኔታ ለቅድመ ዝግጅቱና አሁን ለተገኘው ከፍተኛ ውጤት ትልቅ አስተዋጽኦ እንደነበረው ይገልፃል።

በሀገር አቀፍ ደረጃ ፈተናውን ከወሰዱ ከፍተኛ ቁጥር ካላቸው የማህበራዊ ሳይንስ ተማሪዎች መካከል ከፍተኛ ውጤት ማምጣት የተለየ ስሜት እንዳለው የሚናገረው ሙሉነህ፤ ውጤቱ የጠበቀው ቢሆንም በሀገር አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ውጤት አመጣለሁ የሚል ግምት ግን እንዳልነበረው ነው የሚገልጸው፤ ይህንን ውጤት ለማስመዝገብ የተጠቀመውን ዘዴና መንገድ ሲያስረዳም፤ ከመጀመሪያው ጀምሮ ብሔራዊ ፈተና የሚሰጥባቸውን የትምህርት አይነቶች ቀደም ብሎ ከስር ከስር በማንበብ መዘጋጀቱ ለስኬታማነቱ የተጫወተው ሚና ከፍተኛ ነበር።

``የሐዲስ ዓለማየሁ ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤት መግባቴ አንድ ሁለት ብዬ ተናግሬ የማልጨርሰው ጥቅም አስገኝቶልኛል፤ ወደ አዳሪ ትምህርት ቤት የመግባት ዕድሉ ባይኖረኝና እዛው በተወለድኩበት አካባቢ ትምህርቴን ቀጥዬ ቢሆን ኖሮ በዚህ ደረጃ ውጤታማ መሆን አልችልም ነበር" የሚለው ሙሉነህ፤ የዚህ ምክንያቱ ደግሞ በአካባቢያቸው እንደ አብዛኛው የኢትዮጵያ ክልል አስፈላጊው የመማሪያ ቁሳቁስ ያልተሟላላቸው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መኖራቸውና የ12ኛ ክፍል ፈተና ደግሞ በክፍል ውስጥ ከሚሰጠው የመማር ማስተማር ሂደት በተጨማሪ የበይነ መረብ (ኢንተርኔት) አገልግሎት አግኝቶ ማንበብ ስለሚጠይቅ ነው። በዚህ ትምህርት ቤት ደግሞ ይሄንን አገልግሎት በቀላሉ ማግኘት ስለሚቻል ለውጤታማነቱ ያለው ፋይዳ ከፍተኛ እንደሆነ ይገልፃል።

የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ በአጠቃላይ በተለይ ደግሞ መምህራኖቻችን ይህንን የመሰለ ውጤት እንድናመጣ ለፍተዋል የሚለው ሙሉነህ ፤ ከሁሉም የትምህርት ዓይነት በማድረግ የተለያዩ የማትሪክ ጥያቄዎችን በመስጠት፣ ተምረው ያለፉትን የትምህርት ክፍሎች ደግሞ እንደገና በመከለስ ለፈተናው ብቁ እንዲሆኑ ከፍተኛ ጥረት እንዳደረጉ ይገልፃል።

ፈተናው ከሌላው ጊዜ የተለየና ከባድ ነው የሚባል እንዳልሆነ የሚናገረው ሙሉነህ፤ ጥሩ ዝግጅት ከተደረገ የሚሰራ ፈተና እንደነበር ይገልጻል። በሀገር አቀፍ ደረጃ ለተገኘው ዝቅተኛ ውጤት ምክንያት ነው የሚለውን ከእነርሱ አካባቢ ሁኔታ አንፃር አይቶ ተማሪ ሙሉነህ ሲናገር፤ አብዛኛው ተማሪ ለፈተናው የሚመጥን ዝግጅት አለማድረጉና ከቤተሰብ ተለይተው ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በአቅራቢያቸው ወዳለ ከተማ ልጆች ስሄዱ የሚቆጣጠርም ስለማይኖር ጊዜያቸውን ያለ አግባብ ማባከናቸውና ለተለያዩ አልባሌ ነገሮች ተጋላጭ መሆናቸው፣ በተጨማሪም በ2014 ዓ.ም በነበረው ውጤት ተስፋ መቁረጣቸው የስነልቦና ዝግጅት ማድረግ አለመቻላቸው ነው ይላል፤ ዝግጅት ማድረግ የሚገባው በፈተናው የመጨረሻ ዓመት ብቻ ሳይሆን ከዘጠነኛ ክፍል ጀምሮ ነው፤ ነገር ግን ብዙ ቁጥር ያለው ተማሪ ተገቢ ዝግጅት አላደረገም ይላል።

የመምህራን አቅም ማነስና በተለይ በገጠሪቱ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ያለው እጅግ ዝቅተኛ የትምህርት መሰረተ ልማት በአንፃራዊነት የትምህርት አቀባበላቸው

ውጤቱ የጠበቀው ቢሆንም በሀገር አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ውጤት አመጣለሁ የሚል ግምት ግን እንዳልነበረው ነው የሚገልጸው፤

ጥሩ የሆኑ ተማሪዎች ቢኖሩም እነርሱን የሚያግዝ ምቹ ሁኔታ ባለመኖሩ ያላቸውን አቅም አውጥተው ውጤታማ መሆን እንዳይችሉ ትልቅ ማነቆ እንደሆነባቸው ይናገራል።

የአብዛኛዎቹ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ልክ እንዳልሆነና በውጤታቸውም ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ከፍተኛ እንደሆነ የሚናገረው ሙሉነህ፤ የእርሱ የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ምን ይመስል እንደነበር ሲናገር፤ ከ 9ኛ ክፍል እስከ 10ኛ ክፍል የማህበራዊ ሚዲያን መረጃ ለማግኘትና ለትምህርት አጋዥ ለሆኑ ነገሮች ይጠቀም እንደነበር ከ11ኛ ክፍል በኋላ ግን ሙሉ በሙሉ በማቆም ሙሉ ትኩረቱን የፈተና ዝግጅቱ ላይ አድርጎ እንደቆየ ተናግሯል።

እርሱ ያለበት አካባቢ በባለፉት ዓመታት በነበረው የሠላም ዕጦት ምክንያት በእጅጉ ሲፈተን እንደቆየ የሚናገረው ሙሉነህ፤ ለእንደዚህ አይነት ነገር ጆሮ ባለመስጠት ትምህርቱ ላይ ብቻ ማተኮሩና ማህበራዊ ሚዲያ ከመጠቀም መታቀቡ በጦርነትና ግጭት ዜናዎች ሳይረበሽ ለትምህርቱ ብቻ ጊዜውን በመስጠት ውጤታማ መሆን እንደቻለ ይናገራል።

ትምህርት ትጋትና ጥናት ይጠይቃል የሚለው ተማሪ ሙሉነህ፤ ሁሉም ሰው ካሰበው ዓላማው እስኪደርስ መታገል አለበት ወጣ ገባ የማለት ሁኔታ ካለ ተስፋ መቁረጥ ይመጣል ውጤታማ መሆን አይቻልም ተማሪ ከሆንን አስቀድመን በራሳችን መስራት እንደምንችል አምነን እራሳችንን ከመጀመሪያ ጀምሮ መቅረፅ አለብን ይላል።

ከእሱ ተሞክሮ ተነስቶ የሚናገረው ሙሉነህ፤ በትውልድ አካባቢው ያሉ ሌሎች ጓደኞቹ በትምህርት እስከ መጨረሻው ገፍተው እንዳይጓዙ የሚያደርገው ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ችግር መሆኑንና እሱ ግን አዳሪ ትምህርት ቤት መግባቱ በተለይ በገንዘብ በኩል የሚያጋጥሙ ፈተናዎችን ከመጋፈጥ እንዳዳነው ይናገራል። ነገር ግን ምንም አይነት ፈተና ቢኖር ጽናትን ተላብሶ መንቀሳቀስ እንደሚያስፈልግም ይመክራል።

ሙሉነህ ፤ በትውልድ አካባቢው በብዛት ወጣቶች ስምንተኛ ክፍል ከደረሱ በኋላ የተለያየ የኢኮኖሚ ችግር ስለሚገጥማቸው ራሳቸውን ለመቻል ወደ ተለያዩ ከተሞች ሄደው የቀን ሥራ በመስራት ገንዘብ ለማግኘት ጥረት እንደሚያደርጉ ይናገራል፤ እርሱ ይህ ዕድል እንዳያጋጥመው ቤተሰቦቹ በተቻላቸው አቅም ሁሉ ድጋፍ ስላደረጉለትም ስኬታማ ለመሆን እንዳበቃው ይናገራል።

የፈተና አሰጣጥ ሂደቱ ከዚህ ቀደም ባሉ ጊዜያት እንደነበረው ለስርቆት ተጋላጭ አለመሆኑ ጥቂት ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች ብቻ ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እንዲያልፉ ምክንያት እንደሆነ ተናግሮ፤ ተማሪው የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና በሚጠይቀው ልክ ዝግጅት እንዳላደረገ ይናገራል።

ሙሉነህ ሲናገር፤ ብሔራዊ ፈተና ከክፍል የፈተና ሂደት የሚለየው የአራት ዓመት ትምህርት አካቶ ሰፋ ባለ መልኩ የሚወጣ ነው። ሳምንታት ተዘጋጅቶ በብሔራዊ ፈተና ውጤታማ መሆን አይቻልም ፈተናው የሚለካው የተማሪውን የዓመታት ልፋቱን ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ የብዙዎች ዝግጅት ቸልተኝነት የተሞላበትና ለውጤት የሚያበቃ አልነበረም እነዚህ ጉዳዮች ለተገኘው እጅግ ዝቅተኛ ውጤት እንደ ምክንያት የሚጠቀሱ እንደሆነ ያስረዳል።

``ሙሉ ጊዜዬን በመስጠት አንብቤ ውጤታማ መሆን እችላለሁ የሚል የስነልቦና ዝግጅት ያስፈልጋል፤ ምንም ጥርጥር የለውም ከተነበበ ውጤት ይመጣል፤ ነገር ግን ይህንን ሀሳብ ለራስ መንገርና ሞራል ማዘጋጀት የግድ ነው። ስለዚህ በሁሉም ነገር እራስን ብቁ አድርጎ መዘጋጀት ያስፈጋል" ብሏል።

አንድ ተማሪ ውጤታማ የሆነበት የአጠናን ስልት ለሌላው ላይሰራ እንደሚችል የሚናገረው ሙሉነህ፤ የማህበራዊ ሳይንስ ትምህርት አይነቶች የሆኑትን የታሪክና የጂኦግራፊ ትምህርቶችን ለአብነት ጠቅሶ፤ እነዚህ የትምህርት አይነቶች ረዥም ጊዜ ማንበብና ያነበቡትን እንደገና መከለስ የሚጠይቁ ናቸው። ስለዚህ ቢያንስ ሁለት ዓመት ሙሉ ለብሔራዊ ፈተናው ብቻ ትኩረት ሰጥቶ ማንበብ እንደሚጠይቅ ይናገራል።

ተማሪ ሙሉነህ፤ የተለያዩ የትምህርት አይነቶችን ደጋግሞ ከማንበብ ባሸገር ከዚህ ቀደም የነበሩ የብሔራዊ ፈተና ጥያቄዎችን በመስራት ዝግጅት ሲያደርግ እንደቆየ ገልጾ፤ በዚህ ሂደት አንብቦ ካልሸፈናቸው የትምህርት ዓይነቶች የመጡ ጥያቄዎች እንደነበሩ በመገንዘብ ድጋሚ ክለሳ በማድረግ እያንዳንዱን ምዕራፍ በማዳረስ መጨረሻ ላይ መጨናነቅ በሌለው ሁኔታ ለፈተናው እንደተቀመጠ ይናገራል።

ወደፊት የኢኮኖሚክስ ትምህርት በመማር ራሱን ቤተሰቡንና ሀገሩን መጥቀም እንደሚፈልግ ገልጾ፤ ለዚህም ያበቃው ዘንድ ይህንን በሁለተኛ ደረጃ የነበረውን ጉብዝና አጠናክሮ እንደሚቀጥል ያብራራል።

ተማሪ ሙሉነህ ባስተላለፈው መልዕክት በሁሉም መስክ ጊዜያችንን የምንጠቀምበት መንገድ ለነገ ስኬታችንም ሆነ ውድቀታችን የሚኖረው ሚና ከፍተኛ ነው። ማሳካት ለምንፈልገው ነገር ጊዜ ከምንም በላይ ትልቁና ወሳኙ ነገር በመሆኑ፤ ሁሉም ተማሪ አንድ ጊዜ ካለፈ የማይመለሰው መሆኑን መገንዘብ እንዳለበትም አብራርቷል።

# የምድር በረከት

# የወርቅ ልማቱ ፈተናዎችና ተስፋዎች - በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል

ወርቅነሽ ደምሰው



በኢትዮጵያ ከፍተኛ የወርቅ ክምችት ካላቸው እንዲሁም በከፍተኛ ሁኔታ ወርቅ ከሚመረትባቸው ክልሎች መካከል የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ይጠቀሳል። ክልሉ ወርቅ በተለይ በባህላዊ መንገድ በስፋት ይመረትበታል። በወርቅ ልማት በአብዛኛው የተሰማሩት አነስተኛ አምራቾች ናቸው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ቁጥራቸው ጥቂት ቢሆንም በዓለም አቀፍ ደረጃ በወርቅ ልማት ሥራ ከፍተኛ ልምድ ያላቸው ኩባንያዎች በልማቱ መሳተፍ ጀምረዋል።

ክልሉ ወርቅ ለብሄራዊ ባንክ በብዛት በማስገባት ይታወቅ የነበረ ቢሆንም አሁን ላይ በሚፈለገው መጠን እየተመረተ አይደለም። ለዚህም ህገወጥ የወርቅ ማምረትና ግብይት ተግባር አንዱ ምክንያት በመሆን ይጠቀሳል። በዘርፉ የተሰማሩ አምራቾች ሙሉ በሙሉ ወደ ሥራ አለመግባታቸውና ወርቅን ዘመናዊ በሆነ መንገድ በቴክኖሎጂ ታግዞ ማምረት አለመቻልም ሌሎች በምክንያትነት የሚጠቀሱ ናቸው።

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ማዕድን ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ካሚል ሀመድ እንደሚገልጹት፤ ወርቅ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተ ያለ ማዕድን ነው። በክልሉ ወርቅ በባህላዊና በዘመናዊ መንገድ የሚመረት ሲሆን፣ አብዛኛው በባህላዊ መንገድ መመረቱ የወርቅ ምርትን መጠን እንዳይጨምር አድርጎት ቆይቷል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የወርቅ ማዕድን ለሕገወጥ ተግባር የተጋለጠ ሲሆን፣ ክልሉ በመሆን ይህን በወርቅ ማምረትና ግብይት ስራ ላይ እየተፈጸመ ያለውን የኮንትሮባንድ ተግባር ለመከላከል ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው።

የቢሮ ኃላፊው በ2016 በበጀት ዓመቱ ሩብ ዓመት 525 ኪሎግራም ወርቅ ለማምረት ታቅዶ፤ 104 ኪሎ ግራም ወርቅ መመረቱን ይናገራሉ። አፈጻጸሙ ዝቅተኛ መሆኑን ጠቅሰው፣ ለእዚህም ዋናው ምክንያት ኩባንያዎች በሚፈለገው ደረጃ ወደ ሥራ አለመግባታቸው መሆኑን ኃላፊው አስታውቀዋል። ኩባንያዎች በዚህ ክረምት ወቅት እምብዛም የስራ እንቅስቃሴ እንዳላደረጉ ይገልጻሉ። ሌላው አብዛኛው ወርቅ በባህላዊ መንገድ በአነስተኛ አምራቾች የሚመረት መሆኑን ጠቅሰው፣ ይህም የሚመረተውን የወርቅ መጠን አነሰተኛ ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ መሆኑን ነው የተናገሩት። በቀጣይም ሁሉም አምራቾች ወደ ሥራ የሚገቡበት ሁኔታ እየተመቻቸ እንደሆነም አመላክተዋል።

የባለፈው ዓመት የወርቅ ምርት ግኝት አፈጻጸምም እንዲሁ ዝቅተኛ እንደነበር ኃላፊው አስታውሰዋል። በባለፈው ዓመት 3ሺ ኪሎግራም ለማምረት ታቅዶ፤ 478 ኪሎ ግራም ወርቅ ብቻ ማምረቱን ገልጸዋል። አፈጻጸሙም ከ20 በመቶ በታችና በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ነው የተናገሩት ። ይህም የወርቅ ጉዳይ ምን ያህል ፈታኝ ሁኔታ እንደገጠመው ማሳያ መሆኑን ያነሱት ኃላፊው፤ በተለይ ከዶላር መጥፋት ጋር ተያይዞ ሕገወጦች በወርቅ ላይ በመረባረብ ዋጋው ከፍና ዝቅ እንዲልና ምርቱም ከገበያ ውጪ እንዲሆን ማድረጋቸውን አመልክተዋል።

ዓምና የገጠመው ችግር ዘንድሮ እንዳይደገም የቁጥጥር ሥራው ተጠናክሮ ቀጥሏል የሚሉት ኃላፊው፤ አምራቾች ይነስም ይበዛም ለባንክ እንዲያስገቡ የሚያደርግ ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር እየተደረገ መሆኑን አስታውቀዋል። ይህም በዘንድሮው አፈጻጸም ላይ ችግር ይገጠመናል የሚል ስጋት እንዳይኖር የሚያደርግ መሆኑን ተናግረዋል። አምራቾች ያመረቱትን ወርቅ ወደ ባንክ የማያስገቡ ከሆነ ፈቃዳቸውን እስከመሰረዝ ድረስ የሚደርስ ጥብቅ እርምጃ እየተወሰደ መሆኑን ነው ሃላፊው የገለጹት። አምራቾቹ እርምጃ ተወሰዶባቸው ፈቃዳቸው ከተሰረዘ በብዙ መልኩ ኪሳራ ውስጥ እንደሚገቡ ሃላፊው ጠቅሰው፣ ያመረቱትን ወርቅ ወደ ባንክ የማስገባት ግዴታቸውን እንደሚወጡ ይናገራሉ።

እሳቸው እንደሚሉት፤ ወርቅ ለማምረት በአነስተኛ አምራችነት ተደራጅተው ፈቃድ ወስደው ወደ ሥራ የገቡት 373 አምራቾች ናቸው። ከእነዚህ ውስጥ በሥራ ሆነው ምርቱን ለባንክ እያቀረቡ ያሉት 100 ያህሉ ብቻ ናቸው። የተቀሩት ወደ ሥራ የገቡ ቢሆንም፣ አምርተው ለባንክ ለማቅረብ የበቁ አይደሉም፤ የሚቀራቸው ሥራ አለ ይላሉ።

በኩባንያ ደረጃ ወርቅ ለማምረት ፈቃድ የወሰዱት ሁለት ኩባንያዎች መሆናቸውን አቶ ካሚል ጠቅሰው፣ አንዱ በሕገወጥ መንገድ ሲንቀሳቀስ ተገኝቶ ከሥራ ውጭ እንዲሆን ከተደረገ ከስድስት ወራት በላይ አስቆጥሯል ብለዋል።

ኩባንያው ሕጋዊ በሆነ መልኩ ማንኛውንም ባለሙያ /የውጭ ሀገር ዜጋም ቢሆን/ ቀጥሮ ማስራት ሕጉ እንደሚፈቅድለት ጠቅሰው፤ ይህ ኩባንያ ግን በሕገ ወጥ መንገድ የውጭ ሀገር ዜጎች ቀጥሮ ሲያሰራ በመገኘቱና እነዚህ የውጭ ዜጎች በሕገወጥ መንገድ ወርቅ ሲያዘዋዋሩ በመያዛቸው ምክንያት እርምጃው እንደተወሰደበት ተናግረዋል። በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ በክልሉ ወርቅ በሕገወጥ ፣መንገድ ሲዘዋወሩ በተገኙ ከሰላሳ በላይ በሆኑ የውጭ ሀገር ዜጎች ላይ እርምጃ እንደተወሰደባቸው አስታውቀዋል።

የውጭ ሀገር ዜጎች ቀጥረው እንዲያሰሩ ከማዕድን ሚኒስቴር የሚፈቀድላቸው ልዩ አነስተኛ አምራቾች መኖራቸውን የሚጠቅሱት ኃላፊው፤ በሕገወጥ መንገድ ወደ ክልሉ የሚገቡት የውጭ ሀገር ዜጎች በሚፈቅድላቸው አካላት ሽፋን ሾልከው መግባታቸውን በተደረገው ማጣራት ማረጋገጣቸው አመላክተዋል።

ባለፈው ዓመት እንደ ችግር ከታዩት አንዱ የወርቅ ምርት መጠን አነስተኛ መሆን አንዱ እንደሆነ የጠቅሱት ኃላፊው፤ ዘንድሮ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ ያለው የወርቅ ምርትና ምርታማነትን በመጨመር ላይ መሆኑን አመላክተዋል። ‹‹እስካሁን ወርቅ እየተመረተ ያለው ድሮ ቅድመ አያቶቻችንና አያቶቻችን በሚያመርቱበት ባህላዊ መንገድ ነው።›› ሲሉ ጠቅሰው፣ ወቅቱ የደረሰበትን የተሻለ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም የበለጠ ወርቅ ማምረት እንደሚቻል አስታውቀዋል።

‹‹እስካሁን በባህላዊ ዘዴ የሰው ኃይል በመጠቀም አምራቾቹ በራሳቸው ጥረት የሚመርቱትን ወርቅ ነው ለብሄራዊ ባንክ እንዲገባ ለማድረግ የምንቆጣጠረው›› ያሉት ኃላፊው፤ በዚህ መንገድ ምርትና ምርታማነትን የሚጨምሩ ቴክኖሎጂዎችን ከመጠቀም አኳያ እድሉ ውስን መሆኑንም ገልጸዋል። ቴክኖሎጂ መጠቀም የሚችሉ ባለሀብቶች በዘርፉ እንዲሰማሩ የማድረግ እና ከሌሎች ሀገራት ተሞክሮዎች የመውሰድ ውስንነቶች እንዳሉ አመላክተዋል።

ምርትና ምርታማነትን ከመጨመር አንጻር ቴክኖሎጂ እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ጠቅሰው፣ ይህ ባለመሆኑ አሁን ላይ በሚፈለገው ልክ ምርት እየተገኘ እንዳልሆነ ይጠቁማሉ። ‹‹ በህገወጥ ወርቅ ማምረትና ግብይት ላይ ተሰማርተው በቁጥጥር ሥር የዋሉ የውጭ ሀገር ዜጎች ቴክኖሎጂ ተጠቅመው በአንድ ጊዜ ብቻ ያመረቱት የወርቅ ምርት መጠን እኛ ከምናመርተው ጋር ሲነጻጸር በጣም ሰፊ ልዩነት ያለውና አይተነው የማናውቀው አይነት ምርት ነው››ሲሉ የቴክኖሎጂን አስፈላጊትነት አመልክተዋል።

እሳቸው እንደሚሉት፤ ወርቅ በሰው ኃይል ብቻ ተፈልጎ የሚገኝ አይደለም ፤ በቴክኖሎጂ መታገዝን የግድ ይለዋል። ወርቁ የት ቦታ እንደሚገኝ የሚጠቁም ቴክኖሎጂ ያስፈልጋል። ወርቅንና ሌሎች ነገሮች የሚለይ ኬሚካልም ያስፈልጋል።

አሁን ጥቅም ላይ የዋለው ወርቅን ከሌሎች ነገር ለመለየት የሚያስችለው ኬሚካል እንኳን በጥናት በተረጋገጠው መሠረት 30 በመቶ ያህሉን ብቻ የሚያጣራ ነው። 70 በመቶ የሚሆነው ወርቅ አፈር ውስጥ የሚቀር መሆኑን ኃላፊው መረጃዎች ዋቢ አርገው አመልክተዋል። ይህም ወርቅ የወጣበትን ተረፈ ምርት መልሶ የማጠብ አሰልቺ ሥራ እንዲሰራ እያደረገ ነው። ይህንን የሚያሻሽሉት ደግሞ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ናቸው።

በባለፈው ዓመት በጥቁር ገበያ ላይ የወርቅ ዋጋ ከፍተኛ የሆነበት አንዱ ምክንያት ወርቅ የመግዛት አካሄድ የሚከተሉ ሕገወጦች መበራከታቸው መሆኑን ጠቅሰው፣ ከእነዚህ ውስጥ አስመጪና ላኪዎች እንደሚገኙበት አስታውቀዋል። ቀደም ሲል ብሔራዊ ባንክ 35 በመቶ ጭማሪ አድርጎ ወርቅ ይገዛ እንደነበር ኃላፊው አስታውሰው፤ አሁን ላይ እስከ 60 በመቶ ጭማሪ አድርጎ እየገዛ መሆኑን አስታወቀዋል። ሆኖም ግን በጥቁር ገበያ የወርቅ ዋጋ ከዚህ በሚበልጥ ዋጋ እየተሸጠ መሆኑን ተናግረዋል። ዋጋው ከአንድ ሺብር በላይ ልዩነት እንዳለው ጠቅሰው፣ ይህም ሕገወጥነቱ እንዲስፋፋ ማድረጉን ጠቅሰዋል።

ክልሉም የመቆጣጠር ሥራዎቹ አጠናክሮ በመቀጠል በሕገወጥ ግብይት ላይ የተሰማሩ አካላትንም በማደን በቁጥጥር ሥራ እየዋለ መሆኑን ይናገራሉ። ከዚህ በተጨማሪ ዘላቂ መፍትሔ ለማምጣት በመንግሥት በኩል በአሠራር ጋር ተያይዞ የሚነሱ ችግሮች እንደሚፈቱ ጠቁመው፤ የቁጥጥር ሥራውን አጠናክሮ በማስቀጠል በሕገወጥ ላይ ጠበቅ ያለ እርምጃ የመውሰዱ ስራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ኃላፊው አረጋግጠዋል።

ኃላፊው እንዳስታወቁት፤ በፌዴራል ደረጃ የተቋቋመው ግብረ ኃይል የተጠናከረ ቁጥጥር እያደረገ ይገኛል። ይህን ተከትሎም አሁን ላይ መሻሻሎች እየታዩ ናቸው፤ እስከ ማምረቻ ቦታዎች ድረስ በመሄድ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ በመስራት ሰዎች ወርቅ እንዳያሻሹ ለባንክ በማቅረብ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማድረግ ሥራዎች እየተሰሩ ናቸው። ሰዎች በሕገወጥ መልኩ ወርቅ ይዘው ቢገኙ ወይም ወርቅን ከባንክ ውጪ በሌላ በማንኛውም ሕገወጥ መንገድ ሲገዛም ሆነ ሲሸጥ የተገኘ የሚወሰድበትን እርምጃ ማስገንዘብ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ፤ ይህን ሁሉ ተከትሎም ለውጦች መሻሻሎች ታይተዋል።

እሳቸው እንደሚሉት፤ በወርቅ ዙሪያ የሚያጋጥሙ ችግሮች በአብዛኛው በአሠራር የሚፈቱ ናቸው ። አሁን ላይ ለወርቅ ምርቱ ትልቁ ተግዳሮት የሆነው የአመራረት ስራው በቴክኖሎጂ በመታገዝ በኩል ያለበት እጥረት ነው ። በቴክኖሎጂ አለመታገዝ በወርቅ ማምረት ስራ ላይ ከፍተኛ የምርት ብክነት እንዲኖር አድርጓል። ያለው የወርቅ ክምችትና የሚመረተው መጠን እኩል አይደለም። ከሦስት ጊዜ በላይ የተመረተው አካባቢ ላይ እንደገና መፈለግ ሥራ ይሰራል። ይህ የሚያሳየው ደግሞ በቴክኖሎጂ እጦት ምርቱ ለብክነት መዳረጉን ነው ። ከተገኘው ወርቅ 30 በመቶ ብቻ የሚሰበሰብ ፣ሲሆን 70 በመቶ በአፈር ውስጥ የሚቀር ስለመሆኑ ምርቱ ለብክነት ለመዳረጉ ማሳያ ነው።

ሌላኛው ተግዳሮት ለወርቅ ማምረት ሂደት ጥቅም ላይ የሚውለው ኬሚካል እንደሆነ የጠቆሙት ኃላፊው፤ ይህ ኬሚካል ጥቅም ላይ መዋሉ በተለይ ለቀጣዩ ትውልድ ትቶት የሚያልፈው ጠባሳ ቀላል የሚባል አይደለም፤ አካባቢን ከመበከል ባለፈም ስለኬሚካል ያለው እውቀት እምብዛም ካለመሆኑ ጋር ተያይዞ የሚያስከትለው የጎንዮሽ ጉዳት ቀላል አለመሆኑን ይናገራሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ ወርቅን ከሌላ ባእድ ነገር ለመለየት ከኬሚካል ውጪ ሌላ ምንም አይነት አማራጭ ስለሌለ ኬሚካል መጠቀም የግድ ነው። በክልሉ ሁለት አይነት ወርቅ የሚመረት ሲሆን፣ አንደኛው ጠጠር ተፈጭቶ የሚመረት ወርቅ ነው። በተለይ ጠጠር ተፈጭቶ የሚመረተውን ወርቅ ከሌሎች ባእድ ነገሮች ለመለየት ኬሚካል የግድ አይቻልም። ይህ ሲሆን ግን የሚያደርሱት ጉዳት ዝቅተኛ የሆነ ኬሚካሎችን መጠቀም ይመከራል።

አሁን ጥቅም ላይ እየዋለ ያለው ግን ሌላ አማራጭ ባለመገኘቱና የጎንዮሽ ጉዳት እንደሚስከትል እየታወቀ መሆኑን ተናግረዋል። አምራቾቹ ኬሚካሉን ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ እንዲጠቀሙ እየተደረገ መሆኑን አስታውቀዋል። የእጅ ጓንት፣ ማስክና የመሳሰሉትን በማድረግ በጥንቃቄ እንዲጠቀሙ እየተደረገ መሆኑን ጠቅሰው፣ የተጠቀሙባቸውን ቁሳቁስ ጉድጓድ ተዘጋጅቶ እንዲቀበሩ እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

ሌላኛው የወርቅ አይነት ‹‹ደብል›› ወርቅ የሚባለው መሆኑን ጠቅሰው፣ ይህን ማእድን ማጠቢያ ማሽን ውስጥ ብቻ አስገብቶ በማጠብ ብቻ ወርቁ እንደሚመረት ጠቁመዋል። የዚህ ወርቅ አመራረት ከኬሚካል ጋር እንደማይገናኝ ገልጸዋል። ይህ አይነቱ ወርቅ በብዛት እንደማይገኝ አመልክተው፣ በክልሉ በአብዛኛው የሚመረተው ጠጠር ተፈጭቶ የሚመረተው ወርቅ መሆኑን ተናግረዋል።

ኃላፊው በማእድን ልማት በሀገር ደረጃ ጥሩ እንቅስቃሴ እያደረገ ያለ አንድ ኩባንያ በክልሉ ወርቅን ለማምረት መሰማራቱንም ጠቁመዋል። ‹‹ኩምሩክ ማይኒንግ›› የተሰኘው ኩባንያ በክልሉ ወርቅ ለማምረት በ2014 ፈቃድ መውሰዱን ጠቅሰው፣ ኩባንያው በተያዘው ዓመት ሥራ እንደሚጀመርም አስታውቀዋል። ኩባንያው የክልሉን የወርቅ ምርት በመጨመር ረገድ ተስፋ እንደተጣለበትም ገልጸዋል።

በቅርቡ የማዕድን ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሚሊዮን ማቲዎስ በ2016 በጀት ዓመት በማዕድን ዘርፍ ከ500 ሚሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት መታቀዱን መግለጻቸው ይታወሳል። በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ‹‹አላይድ ጎልድ ማይንኒን›› የተሰኘ የአውስትራሊያ የወርቅ አምራች ኩባንያ አካል የሆነው ‹‹ኩምሩክ ማይኒንግ›› ኩባንያ ወርቅ ለማምረት እያከናወነ ያለውን ተግባር በማሳያነት ጠቅሰዋል። ኩባንያው የወርቅ ማዕድን ፍለጋውን መጨረሱን ጠቅሰው፣ ከ500 ሚሊየን ዶላር በላይ በሆነ ወጪ “በኢትዮጵያ ትልቁ የወርቅ ኩባንያ” ይሆናል ተብሎ የሚጠበቀውን ማምረቻ እየገነባ እንደሆነም መግለጻቸው ይታወሳል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## መንታ ነፍስ

በትረ ሙሴ (መልክ ኢትዮጵ)

ኤልሳ የዛሬ 15 ዓመት የማውቃት ሴት ናት፡፡ ይሄን ሁሉ ዘመን ኖራ እንዴት አትረሳኝም..ስለምን አትርቀኝም? እላለው፡፡ ትካዜ የሚደፍረኝ እሷ ባለችበት ትላንቴ በኩል ነኝ፡፡ በእሷ በኩል መጥቶብኝ ትካዜዬን አሸንፌው አላውቅም፡፡

ትውውቃችን እንደዘበት ነበር፡፡ አንድ ማለዳ ነው..በስራ ማጣት ተስፋ ቆርጬ ራሴን እንዴት ላጥፋው? ምን አይነት ሞት ልሙት? እያልኩ ምርጥ ሞት ፍለጋ ላይ እያለሁ፡፡ በዛን አይነት ትውውቅ የቀረቧትን ሴት አለመርሳት ማለት ለእኔ ብቻ ነው የተቻለው፡፡ ለቤተሰቤ ሰባተኛ ልጅ ነኝ፡፡ አባቴ ሁሉንም ልጆቹን ድል ባለ ድግስ አስመርቋል፡፡ ሲያስመርቅ ግን ለእኛ አስቦ ሳይሆን ለራሱ ተጨንቆ ነበር፡፡

አባቴ ከሰይጣን ቀጥሎ ሁለተኛው ተንኮለኛ ሰው ነው፡፡ ሲወልደን ጀምሮ በእኛ በኩል የሚያገኘውን ትርፍ አስልቶ እንደሆነ እኛን አሲዞ በሚቆምረው ቁማር ደርሼበታለው፡፡ ትርፍ ይኑረው እንጂ ምንም ነገር ከማድረግ ወደኋላ አይልም፡፡ ጌታን እንደሸጠው ይሁዳ ብዙ ጊዜ ስሞ ሊሸጠን ሞክሮ አልተሳካለትም፡፡ የሰፈሩን ሰው የሚበዘብዘው በእኛ በኩል ነው፡፡ እንደጉድ በቀጠነ ጠላ፣ እንደ ጉድ በቀጠነ ወጥ፣ ፊትና ኋላው በማይለይ የዘንጋዳ እንጀራ የሚያውቀውንም የማያውቀውንም ጠርቶ ልጆቼን መርቁልኝ ሲል በራሪ ወረቀት ያስልካል። እኔም ሆንኩ ወንድምና እህቶቼ ዩኒቨርሲቲና ኮሌጅ ሶስትና ከዛ በላይ ዓመታትን ስንማር ከአባታችን የተላከ ገንዘብ አናውቅም፡፡ በዓመት አንድ ጊዜ ለእረፍት ስንሄድ ነው አባታችንን በአካለ ስጋ የምናየው፡፡ ከዛ ውጪ ደውሎም ደውለንም አናውቅም፡፡

ምርቃት የማልወድ ብሆንም ከአባቴ ጋር በተደረገ የሁለት ሳምንት ዝግ ሙግት በኋላ ተሸንፌ ድግስ ተደገሰ። እኔ ስራ ፍለጋ ስንከራተት አባቴ ያስገባውን ገቢ ያሰላ ነበር፡፡ በተመረኩኝ በሰልስቱ ስራ ፍለጋ አዲስ አበባን ከእግር እስከራሷ ዞርኳት፡፡ በእኔ እግር የተረገጠችውን ያክል በማንም አልተረገጠችም፡፡ አንድ ቀን ምርር አለኝና..ከዚህ ቤተሰብ (በተለይ ከአባቴ) የሚገላግለኝን ነገር ሳወጣ ሳወርድ አስኮናኝ ፊቱን ይዞ ሞት ፊቴ ድቅን አለ፡፡ ሞት ከመች ጀምሮ ነው አስኮናኝ ፊት ያለው? ሲገልም ሆነ ከገደለ በኋላ ምን እንደሚመስል የማላውቀው መስሎት ነው? እያልኩ በሞት አስኮናኝ ገጽ ስወጣና ስወርድ በተቀመጥኩባት የአስፓልት ዳር ብዙ ቆየሁ፡፡ ሞትን ሞኝህን ብላ ልለው ፈለኩ፡፡ ግን ከእሱ ሌላ የምገላገልበት ሁነኛ መላ ስለሌለ አላልኩትም፡፡ ደሞ ማን ላይ ነው የምታሾፈው? ብሎ አልወስድህም ቢለኝ ምን ይውጠኛል ስል እንዳሻህ አልኩት፡፡

እንዴት ብሞት ይሆን ቀባሪ የሚያዝንልኝ? እንዴት ብሞት ነው በትውልድ ልብ ውስጥ የማልረሳው? እያልኩ ምርጥ ሞት ፍለጋ ላይ ሳለሁ...ከኋላዬ በመጣች በአንዲት ሴት ዜማ በቀላቀለ ሳቅ ተደነቃቅፌ ሞትን ረሳሁት፡፡ ሳቋን በደንብ እንዳጣጣመው በሞት የደከመ አእምሮዬን ላንጠራራ ቀና ስል ከፊት ለፊቴ ሞት አንገቷን ያስደፋት ጥቁር በጥቁር የለበሰች ሴት አየሁ፡፡ ሁለት ደስተኛና ሀዘንተኛ ነፍሶች እኔን መሀል አድርገው ከፊትና ከኋላዬ አስተዋልኩ፡፡ የእናቴ ይሆን መቼም የአባቴ ውቃቢ አይሆንም..ከሞት ሊታደገኝ ሁለት በሞትና ህይወት መከራና ፈንጠዝያ ውስጥ ያሉ ሴቶችን የላከልኝ መሰለኝ። አንድ ልቤን ለጥንድ ነፍሳቸው ሰጥቼ ለሌላ ሀሳብ ተዳረኩ፡፡

ከፊት ለፊቴ ያለችው ሴት ሞት አንገቷን አስደፍቷት፣ ሀዘን ደስታዋን ቀምቷት፣ ባቀረቀረ አንገት አልፋኝ ሄደች። እየመጣ በሚሄድ እንባ፣ አልረሳ ባለ ናፍቆት፡፡ በዛች ሀዘንተኛ ነፍስ ላይ ባለመኖር ውስጥ የታመቀ ናፍቆትና ትዝታ አስተዋልኩ..ሴትነቷን ለሁለት ከፍለውት፡፡ ጀርባዋ ላይ አይኔን ተከልኩ..እንዲመለስ የሚፈልገው ግን ያልተመለሰ የማይመለስም የሆነ ነገር አየሁበት፡፡ እንደነፍሷ ግርጥት ብሏል፡፡ ከንፈሩን እያወዛወዘ አንድ ነገር ሲል አየዋለው..ጀርባዋ፡፡ ደግሞም ያለቅሳል..በጸሞነ ለቅሶ እንባውን እያዘራ ላትመለስ የሄደችን አንዲት ነፍስ ይከጅላል፡፡

ወደ ነፍሴ የሆነ ነገር ተማገደ፡፡ በነፍሷ ነፍሴን ያሻርኩ መሰለኝ፡፡ ሞት የሚሉት ሀሳብ ከሆዴ ውስጥ ብን ብሎ ሲወጣ ታወቀኝ፡፡ በሀዘንተኛዋ ሴት ከሻትኩት ሞት ተቆራረጥኩ፡፡

ወደ ሳቂታዋ ሴት አዘነበልኩ፡፡ ሞትን ንቃ፣ ህይወትን ናፍቃ ታስካካለች፡፡ ከድምጽዋ ኩሬ ውስጥ የሚፈልቅ የአጥቢያ መሳይ እግዚኦታ ነፍሴን አረሰረሳት፡፡ በእሷ በኩል መኖር ከጀልኩ..ሞትን የት አባትክ አልኩት። ከአንደበቷ ዋሻ የሚነሳውን አንቂ ድምጽዋን ሳታየኝ ሰማሁት፡፡

ወደ ሀዘንተኛዋ ሴት ቀና አልኩ...እንዳቀረቀረች በርቀት አየኋት፡፡ ጀርባዋ አሁንም አልሻረም እንደተሰበረ ነው፡፡

ከተቀመጥኩበት ተፈናጥሬ ወደጀርባዬ ዞርኩ፡፡ ባላየት ያስመኘኝን እጹብ ውበት ልጅነትን በተሻገረ ፊቷ ላይ አየሁት፡፡ ከድምጽዋ ማማር ተንቀሳቃሽ በቤተክሲያን መሰለቸኝ፡፡ ቄስና ገበዝ ይዛ ይዛ የምትዞር፡፡ ብቻዋን ናት። ይሄን ሁሉ ወሬ ከማን ጋር ስታወራ እንደነበር ግራ ገባኝ፡፡ መንፈስ መሰለችኝ፡፡ ላማትብ የመስቀል ቅርጽ የሰራ ጣቴን ወደ ግንባሬ ስሰድ አጠገቧ ትንሽዬ ቡችላ አየሁ..እግሯ ላይ እየተንደባለለ ሰርከስ እየሰራ፡፡ በእድሜ እንደምትበልጠኝ ወጣትነትን የሸሸ ፊቷ ነገረኝ፡፡

ወዳለችበት ሄጄ እሷንም ጓደኛዋንም እጅ ነሳኋቸው። ከእሷ ቀድሞ ፈጣን ቡችላዋ ጭራውን ቆላልኝ፡፡ እኛ ሰዎች ሁልጊዜም በውሻ እንደተበለጥን ነው፡፡

‹እዚህ ሰፈር ነሽ? የመጀመሪያ ቃሌን በጥያቄ ጀመርኩ፡፡

‹አይደለሁኝም..

‹እና ያለሰፈርሽ፣ ለዛውም ሰው በር ላይ በወንጀል እንደምትጠየቂ አታውቂም? ስል የማውቀውን ከማላውቀው ጋር ቀላቅዬ ዘላበድኩ፡፡

‹ፍቅር ሲመራን ጠላቶቻችን ላይ ድንጋይ ለመወርወር አቅም አናገኝም፡፡ የእኔ እዚህ መቆም ሌሎችን እንደማያስከፋ ርግጠኛ ስለሆንኩ ነው የቆምኩት› አለችኝ፡፡ እኔ ብሆን የተጠየኩት ከመኖር ውጪ ምንም ቢያደርጉኝ በደስታ ነው የምቀበለው እል ነበር፡፡

‹ድካምሽን በማረፍ ነው የምታሳልፊው? ስል ድንገተኛ ጥያቄ ሰነዘርኩ፡፡

ራሷን እየነቀነቀችልኝ ‹ሲደክመኝ በማረፍ ነው የምበረታው፡፡ ደክሞኝ መቆምን አስቤው አላውቅም› ስትለኝ ባህር ከከፈለው ሙሴ ጋር የማወራ ነበር የመሰለኝ፡፡

‹መኖር ታክቶኛል፣ መኖር የሚያስናፍቅ ምን አለሽ? አልኳት እንደቀልድ፡፡

‹እኔ ለአንተ የሚሆን ምንም የለኝም፡፡ ሁሉም ሰው ከአንተ ቀጥሎ ነው ለአንተ፡፡ ለአንተ ከአንተ የቀደመ ማንም የለም፡፡ በራስህ ላይ ሌሎችን ፊተኛ ስታደርግ ወደኋላ እየቀረህ ነው፡፡ እናም ራስህን አንቃው› አለችኝ፡፡

በድን ሆኜ ስሰማት ነበር፡፡ እንደዛ በሚያማምሩ ቃሎች፣ ሞገስ በሚሰጡ አንደበቶች ማንም ተናግሮኝ አያውቅም፡፡ ካንቀላፋሁበት ስነቃ ታወቀኝ፡፡

‹የደስታ በሮችህ መቼም እንዳይከፈቱ አድርገህ ከዘጋሃቸው መቼም አይከፈቱም፡፡ መቼም እንዳይዘጉ አድርገህ ከከፈትካቸውም መቼም በማንም አይዘጉም። በሮችህን ዘግተህ ቁልፉን አርቀህ ወርውረህ ያን በር ማን የሚከፍትልህ ይመስልሀል? መጀመሪያ በሮችህን ላለመዝጋት ሆነህ ኖር፡፡ ከዘጋሃቸው በኋላ ንፋስ እንዲያስገቡ ትንሽ ገርበብ አድርጋቸው፡፡ በዛ ገርባባ በር የሚገባ ስለሚኖር›

ስትለኝ..

ለዘመናት ከተላመድኩት የአለመኖር ሱስ ራሴን ስመነግል፣ ከአባቴ ውቃቢ ስቆራረጥ ራሴን በራሴ ውስጥ አገኘሁት፡፡

‹ማንም ለአንተ ከአንተ ቀጥሎ ነው፡፡ የደስታህ ፊተኛ፣ የስኬትህ ቀዳማይ አንተ ነህ፡፡ ሌሎች እንዲያሻግሩህ፣ ሌሎች እንዲመሩህ አትፍቀድ እንደዛ ካሻህም አእምሮና ልብህን ከፍተህ ይሁን፡፡

ዝምታ ወረሰኝ..አሁን ብቻ አይደለም ከዚህ በኋላም እሷን ሳስብ ዝም የምል ይመስለኛል፡፡ የሚነፍሰው ንፋስ ወሬዋን እንዳይሻራርፍብኝ በተጠንቀቅ ቆሜ ሰማኋት፡፡

‹ራስህን የትም አትሻው..በአንተ ውስጥ ስላለ በአንተ ውስጥ ፈልገው፡፡ መከራዎችህን በሞት ለመርሳት አትሞክር፡፡ ሕይወት እንጂ ሞት መቼም አለ፡፡ እናም ትግልህ ብርሀን እስኪያሳይህ ድረስ መከራህን ናቀው። ቀኖች በሰው ልጅ ልክ ተከፋፍለው ነግተው የሚመሹ ናቸው፡፡ በዙሪያችን ያሉ ደስተኛና ስኬታማ ሰዎች በነሱ ቀን ላይ እንደሆኑ ልብ በል፡፡ ቀንህ እስኪመጣ በትዕግስት መጠበቅ ነው› አለችኝ፡፡ የመጨረሻ ወሬዋ ባልሆነ እያልኩ ስሰጋ ‹ደህና ሁን› የሚል የስንብት ድምጽዋን አስከተለች፡፡

# ዓለም አቀፍ

## በእስራኤል እና ፍልስጤም ጉዳይ የአሜሪካ እና ሩስያ ሃሳቦች ውድቅ ተደረጉ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የእስራኤል እና ፍልስጤም ግጭትን ለማቆም በአሜሪካ እና ሩሲያ የቀረቡ ረቂቅ የውሳኔ ሃሳቦች በተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክር ቤት ውድቅ ሆነዋል።

የምክር ቤቱ አባላት በመጀመሪያ ድምጽ የሰጡት አሜሪካ ባቀረበችው ረቂቅ የውሳኔ ሃሳብ ላይ ነው።

የውሳኔ ሃሳቡ በጋዛ የሰብዓዊ ድጋፍ ቆም እንዲል የሚጠይቀውን እና በእስራኤል ላይ የፍልስጤም ቡድን ሃማስ ያደረሰውን ጥቃት በማውገዝ በሃማስ የተያዙትን የተቀሩትን ታጋቾች በሙሉ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በአስቸኳይ እንዲፈቱ የሚጠይቅ ነው።

የውሳኔ ሃሳቡ 10 ድምጽ ድጋፍ ያገኘ ሲሆን፤ ሩሲያ፣ ቻይና እና የተባበሩት አረብ ኢምሬትስ ተቃውመውታል።

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአሜሪካ ተወካይ ሊንዳ ቶማስ ግሪንፊልድ ሩሲያ እና ቻይና የውሳኔ ሃሳቡን መቃወማቸው "ሀገራቸውን በጣም አሳዝኗል" ብለዋል።

ለሰብዓዊ ድጋፍ አፋጣኝ የተኩስ ማቆምን የሚጠይቀው የሩስያ ረቂቅ የውሳኔ ሃሳብ ደግሞ በቂ ድምጽ ባለማግኘቱ በፀጥታው ምክር ቤት ውድቅ ተደርጓል።

የውሳኔ ሃሳቡ አራት የድጋፍ፣ ሁለት ተቃውሞ እና ዘጠኝ ድምጸ ተአቅቦ አግኝቷል። አሜሪካ እና ዩናይትድ ኪንግደም የውሳኔ ሃሳቡን ተቃውመውታል።

የሩስያ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ተወካይ ቫሲሊ ኔቤንዚያ የፀጥታው ምክር ቤት በመካከለኛው ምስራቅ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ለተፈጠረው ችግር ምላሽ ለመስጠት ሌላ እድል መጠቀም ባለመቻሉ ሩሲያ ተጸጽታለች ብለዋል።



የፀጥታው ምክር ቤት በ10 ቀናት ውስጥ በእስራኤል እና ፍልስጤም ያለውን ሁኔታ አስመልክቶ ባለፈው ሳምንት በብራዚል እና ሩሲያ የቀረቡ ሁለት የተለያዩ ረቂቅ የውሳኔ ሃሳቦች ውድቅ ማድረጉ ይታወሳል ሲል የዘገበው አናዶሉ ነው።

## በወርቅ ማዕድን ጉድጓድ በገዛ ባልደረቦቻቸው ታግተው የነበሩ ሠራተኞች ተለቀቁ

በጋዜጣው ሪፖርተር

በደቡብ አፍሪካ በወርቅ ማውጫ ጉድጓድ በባልደረቦቻቸው ለቀናት ታግተው የነበሩ ወርቅ ቆፋሪዎች ተለቀቁ። የወርቅ ማዕድን አውጪዎቹ ላለፉት ሦስት ቀናት በመጥፋታቸው በደቡብ አፍሪካ ጉዳዩ አነጋጋሪ ሆኖ ነበር።

አጋቾቹ ልዩ ልዩ ከቁፋሮ ጋር የተያያዙ መሣሪያዎችን በመያዝ ታጋቾቹን አስፈራርተዋል ተብሏል። ጎልድዋን በሚባለው የማዕድን ቁፋሮ ማዕከል ነው ክስተቱ የተፈጠረው።
ከእገታው አምልጠን ነው የወጣነው ካሉት መካከል አንዱ ‘ሕይወቴን ለማዳን ነው ማምለጥ የቻልኩት’ ሲል ለቢቢሲ ተናግሯል።

ነገሩ ይበልጥ አነጋጋሪ ያደረገው አጋቾቹ የታጋቾች የገዛ ባልደረቦቻቸው መሆናቸው ነው። እገታው ሊፈጸምባቸው የቻለውም የሠራተኛ ማኅበር ምሥረታ ላይ አለመግባባት በማጋጠሙ ነው።

የብሔራዊ ማዕድን አውጪዎች ማኅበር አጋቾቹን ‘አደገኛ ቦዘኔዎች’ ሲል አውግዟቸዋል። አጋቾቹ ናቸው የሚባሉት ደግሞ የዚህ ሠራተኛ ማኅበር ተቀናቃኝ የሆነው የደቡብ አፍሪካ የማዕድን እና ኮንስትራክሽ ሠራተኞች ማኅበር አባላት ናቸው።

ከጆሀንስበርግ በቅርብ ርቀት በሚገኝ ግዙፍ የወርቅ ማዕድን ማውጫ ጉድጓድ ውስጥ የተፈጸመው እገታ ላለፉት ሦስት ቀናት ቤተሰቦችን ሲያስጨንቅ ነበር የሰነበተው። ሠራተኞችን አግቷል ተብሎ ወቀሳ የደረሰበት የሠራተኛ ማኅበር በበኩሉ ድርጊቱን አለመፈጸሙንና ታገትን ያሉትም በገዛ ፈቃዳቸው አመጽ ላይ እንደነበሩ ተናግሯል።

ከጉድጓዱ ከሦስት ቀናት በኋላ አምልጠን ወጣን ያሉ ቆፋሪዎች ለቢቢሲ ሲናገሩ ነገሩ ለሕይወታቸው ጭምር አስጊ ነበር ብለዋል።

የ32 ዓመት ታጋች በመጀመርያ ቀን ምግብ ነበር፤ በሁለተኛው ቀን ከመጀመርያ ቀን የተረፈውን ምግብ ተቋደስን ሲል ለቢቢሲ ተናግሯል።
ቀጥሎ በነበሩት ቀናት የሚላስ የሚቀመስ በመጥፋቱ በውሃ ብቻ ነፍሳቸውን እንዳተረፉ አንድ በጎልድዋን ለ10 ዓመት የሠራ ታጋች ተናግሯል።

በሁለቱ የሠራተኞች ማኅበር መካከል አለመግባባቱ የተፈጠረው ሠራተኞችን በማገት የተጠረጠረው ማኅበር ሕጋዊ እውቅና ስለሌለው ነው። ሕጋዊ እውቅና ለማግኘት ያደረጋቸው ሙከራዎችም አልተሳኩለትም።

የማዕድን ቆፋሪ ሠራተኞች ቤተሰቦች ለቀናት ወደ ሥፍራው በመሄድ በድንኳን ውስጥ ውለው እያደሩ የታጋቾችን መለቀቅ በትዕግስት ሲጠብቁ ነበር።

የፖሊስ ሕዝብ ግንኙነት ብሬንዳ ሙዲሪ ከጉድጓዱ የወጡ ማዕድን ቆፋሪዎችን ውስጥ ስላለው ሁኔታ መረጃ እየጠየቅናቸው ነው ብለዋል። አጋቾቹ 15 እንደሚደርሱ ተጠቁሟል።

## ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም

# ችሎታና ፍላጎትን ያማከለ ምደባ

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

ዘመን የሚለውን ቃል አውዳዊ ፍቺ በመስጠት ምሁራን በተለያየ መንገድ ይገልፁታል። አንደኛው ልኬት ነው ሲል፤ ሌላው ሰንሰለት ይለዋል። አንዳንዱ ደግሞ በትውልዶች መካከል ያለ የሁነት ለውጥ ሲል ይተረጉመዋል። ሆነም ቀረ አንድ ነገር ሁሉንም የሚያስማማ ይመስላል። በሰዎች የሥራ እንቅስቃሴ ውስጥ ጊዜን መሰረት ያደረገ የትውልድ ለውጥ የሚለው። ትውልዱ በባህሪ፤ በእድገት ዘመን እየቆጠረ ልዩነቱን ሊያሳይ ይችላል። ለአብነት የአሁኑን ዘመን ብቻ ብናነሳ ከትናንትናው በቴክኖሎጂ አጠቃቀሙ በብዙ መልኩ ይለያል። ብዙ ሳይደክም ስራዎችን ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ በቀላሉ ያከናውናል፤ ጊዜውን ይቆጥባል። ይህ ደግሞ ተጨማሪ ሥራ ሳይቀር እንዲሰራ ያግዘዋል። ትርፋማነት፤ ውጤታማነትም በዚያው ልክ ይጨምራል።

ለዛሬ ይህንን እንድናነሳ ያስገደደን ነገር የዩኒቨርሲቲዎች ምደባ ትናንትና ዛሬን ለማየት ስለወደድን ነው። ትናንት ቴክኖሎጂው ሳይኖር ምደባ ሲካሄድ ምን አይነት ክፍተቶች ነበሩ፤ ቴክኖሎጂው በመምጣቱ ምን ምን ነገሮች ቀለሉና መሰል ነገሮችን በዛሬው አምዳችን ልናስቃኛችሁ ፈልገናል።

ትናንት ዩኒቨርሲቲ የሚገቡ ተማሪዎች ምደባ የሚካሄደው በቀጥታ በሰዎች አማካኝነት ስለነበር ለዘመድ፤ ለስልጣንና ለገንዘብ ቅድሚያ የሚያሠጡ ሁኔታዎች ምቹ ነበሩ። የተማሪዎች ምርጫ እነዚህን ተንተርሶ የሚሰራ ሲሆን፤ በዚህ ደግሞ ዩኒቨርሲቲዎች በአቅም ተማሪዎችን የማስተማሩ ሁኔታ ሲፈትናቸው ታይቷል። ተማሪዎችም የገቡት በአቅማቸው በሚመጥናቸው ዩኒቨርሲቲ ባለመሆኑ በብዛት ሲባረሩ፤ ሲጨናነቁና የህሳባቸውን ሲሞሉ አይታይም። እንዲያው ለስሙ እንኳን ተመርቀው ቢወጡ ተገቢውን እውቀት አይጨብጡምና በስራ ቅጥርም ሆነ በተለያየ መልኩ ሲቸገሩ ይስተዋላል።

ጎበዙ ተማሪ የሚፈልገውንና ችሎታውን የሚያረጋግጥለት ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ባለመግባቱ ብዙ ነገሮችን ያጣል። በአቅሙ ልክ እንዳይሰራና ተወዳዳሪ የሚሆንበትን እድል እንዲያገኝ ይገደባል። ዓመታት የተቆጠሩት በዚህ አይነት መልኩ እነደነበርም ማንም አይዘነጋውም። ሁሉም ሰው የትምህርት ስርዓቱ ወድቋል፤ ያልተማረው ተማሪ እየተመረቀ ሥራዎች እየተበላሹ ነው መባባሉም ሰፍቶ እንደነበር ይታወቃል።

ይህ ጥያቄ በመጠኑም ቢሆን ምላሽ ያገኝ ዘንድ መንግስት የተለየ ስትራቴጂ መከተል እንደሚጀምር ከሰሞኑ የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ የሩብ ዓመቱን አፈጻጸም ለተወካዮች ምክርቤት በአቀረቡበት ወቅት ተናግረዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ መንግስት የትምህርት ዘርፉን እያዘመነ በመምጣቱ ምደባ ዘመናዊ እና ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነት ባለው ማሽን እንዲሰራ ተደርጓል። ይህ ደግሞ ምደባው ሲካሄድ በዋነኝነት የተማሪዎችን ውጤት መሰረት ባደረገ መልኩ መከናወኑ ነው። ይህ ሲደረግ ደግሞ መጀመሪያ የሚከናወነው ተግባር ምደባውን ለሚያከናውነው ማሽን የምደባ ግብዓቶችን መስጠት ነው። እነዚህም ከመቁረጫ ነጥብ በላይ ያመጡ ተማሪዎች ስም ዝርዝር፤ የዩኒቨርሲቲዎች የመቀበል አቅም፤ የመቁረጫ ነጥብ የተማሪዎች ውጤት፤ ምድብ የሚሉት ሲሆኑ፤ ማሽኑ በሚሰጠው የስም ቅደም ተከተል ምደባው የሚከናወን ይሆናል። ይህ ደግሞ በተለይም በጣም ጥሩ ውጤት ያመጡ ተማሪዎችን ተጠቃሚ ያደርጋል። በዩኒቨርሲቲም ሆነ በትምህርት መስክ የመጀመሪያ ምርጫቸውን አግኝተው ለቤተሰባቸውም ለሀገራቸውም አለኝታ የሚሆኑበትን እድል ይሰጣቸዋል።

ዘንድሮ ደግሞ በማሽን መመደቡ እንዳለ ሆኖ አንድ ለየት የሚያደርግ ነገር እንደመጣ የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ያነሱ ሲሆን፤ ይህም የዘንድሮ የዩኒቨርሲቲ የተማሪዎች ምደባ ችሎታና ፍላጎታቸውን መሰረት ባደረገ መልኩ የሚከናወን መሆኑ ነው። ምክንያቱም ማሽን ምደባውን ቢሰራውም ከምደባው በኋላ የተለያዩ ጣልቃ ገብነቶች እስከዛሬ ነበሩ። ይህ ደግሞ የተማሪዎችን ችሎታና ፍላጎት ብቻ ሳይሆን የሚገድበው የሌሎችን ተማሪዎች እድል ጭምር ይዘጋ እንደነበር በተለያየ አጋጣሚ መታየቱን አብራርተዋል። እናም እሳቸው እንዳሉት ዘንድሮ ተማሪዎች የፍላጎታቸውን በውጤታቸው መሰረት ያገኛሉ። በማንም ተጽዕኖ የሚቀየር ነገር አይኖርም።

እንደ ሚኒስትሩ ማብራሪያ ከሆነ፤ በ2014 የትምህርት ዘመን በመንግስትና በግል የሪሚዲያል ፈተና ከወሰዱ 145 ሺህ ተማሪዎች መካከል 90 ሺህ ያህሉ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መግባት የሚያስችላቸውን ውጤት አስመዝግበዋል። እነዚህ ተማሪዎች በ2015 የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ወስደው የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ውጤት ካመጡት ከ27 ሺህ በላይ ተማሪዎች ጋር ተደምረው በአጠቃላይ ከ117 ሺህ በላይ ተማሪዎች ወደ ተለያዩ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ይመደባሉ። ምደባውም ከላይ እንደተባለው በችሎታቸውና በፍላጎታቸው መሰረት ይሆናል። በፍትሐዊነት ሁሉም የሚጠቀሙበትን መንገድ ተከትሎ እንዲሰራም ይደረጋል።

ቀደም ሲል በተማሪዎች ምደባ ላይ ይነሱ የነበሩ ቅሬታዎችን ታሳቢ በማድረግ ክፍተቶች ተለይተው እንዲስተካከሉ መደረጉን ያብራሩት ፕሮፌሰር ብርሃኑ፤ ይህ መሆኑ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የትምህርት ጥራትን ለማምጣት ያስችላል። ተማሪዎች በችሎታቸውና በፍላጎታቸው ላይ ተንተርሰው ሲማሩ ደግሞ ውጤታማ የመሆን አማራጫቸው ይሰፋል። በተማሪዎች ላይ ተጨባጭ የውጤት መሻሻል በስፋት እንዲታይ ያደርጋል።

ከምንም በላይ ደግሞ ፍላጎትንና ችሎታን ያማከለ ምደባ ሲከናወን የትምህርት ስታንዳርዱ ጭምር ይስተካከላል። ምክንያቱም ሞጋች ተማሪዎች ይፈጠራሉ፤ ባሕላቸውን አክባሪና አመለካከታቸው መልካም ስብዕናን የተላበሰም ይሆናል። ዕውቀት፣ ችሎታ መሰረታዊ መገለጫቸው የሆኑ ተማሪዎች ይበራከታሉ። ኃላፊነት የሚሰማው፤ ተነሳሽነትና ነፃነት ያለው ተማሪም ይሆናሉ። ይህ ደግሞ እንደ ሀገር ያለውን ችግር ከመፍታት አኳያ የማይተካ ሚናን ይጫወታል። የትምህርትም ዋነኛ ግቡ ይህ ነውና መሰረታዊ ለውጥ ያመጣል።

ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ እንዳሉት፤ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ሁሉም ኢትዮጵያዊ በእኩል የሚገለገልባቸው ተቋማት ናቸው። ስለዚህም ይህንን ስብዕናና መልካም መንገድ እንዲያገኙ ከማስቻል አኳያ ምደባውን ከማንኛውም ተጽዕኖ ነጻ ማድረግ የግድ ነው። ማንኛውም አካል ስልጣኑን ተጠቅሞ የተለየ ጥቅም ለማግኘት መሞከር የለበትም። ለዚህ ደግሞ የትምህርት ሚኒስቴር አቋም አንድና አንድ ነው። ይህም የሕክምና ክትትል እያደረጉ መሆኑን ትክክለኛ ማስረጃ ከሚያቀርቡ ተማሪዎች ውጪ የዝውውር ጥያቄ ተቀባይነት አይኖረውም። ስለዚህም ሁሉም ሰው ይህንን አውቆ ትብብር ሊያደርግ ይገባል። ከማስቸገርም ራሱን ነጻ ማድረግ አለበት።

ችሎታና ፍላጎትን ያማከለ ምደባ ለትምህርት ጥራቱ መሰረታዊ ለውጥን ያቀዳጃል የሚሉት ፕሮፌሰሩ፤ በምደባ ብቻ ሳይሆን በዩኒቨርሲቲዎች ልየታም ይህ ነገር ተጠናክሮ ይቀጥላል። ሁለቱ ነገሮች በአንድነት ሲመጡ ደግሞ ሀገር የምትፈልገውን የተማረ የሰው ኃይል በእጅጉ ማሳካት ይቻላል። ጥሩ መሪ፤ ጥሩ አስተማሪና ጥሩ ተማሪም በሁሉም መስክ ይፈጠራል። እናም ይህ እስኪሳካ ድረስ በተለያየ መልኩ ጥረቶች የሚደረጉ ይሆናል ሲሉም አብራርተዋል።

## ከከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ የግል ዘርፉን የማሳተፍ አስፈላጊነት

የከተማና መሠረተ-ልማት ሚኒስቴር ከተሞች ውብና ጽዱ ሆነው ለነዋሪዎቻቸው፣ ለኑሮና ለስራ ምቹ እንዲሆኑ በትኩረት እየሰራ ይገኛል። ከተሞች ውብና ጽዱ እንዲሆኑ ደግሞ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ስራ ቁልፍ ጉዳይ ነው። በመሆኑም ዘርፉ የሚመራበትን የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስትራቴጂ በ2006 ዓ.ም አውጥቷል። እንዲሁም የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስታንዳርድን ደግሞ በ2007 ዓ.ም በማዘጋጀት ከተሞቹ ዘርፉን በአሰራር ስርዓት እንዲመሩት ለማድረግ ብዙ ስራ ተሰርቷል። አሰራሩም በሁሉም ከተሞች በተለይ ከ 20 ሺህ በላይ ሕዝብ ባላቸው ከተሞች እንዲተገበር ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር የተለያዩ ስራዎችን ይሰራል።

በሚኒስቴር መ/ቤቱ ስር የተቋቋመው የከተሞች የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖ መቋቋሚያ ቢሮ ደግሞ በዋናነት የዘርፉን ኃላፊነት ወስዶ ለከተሞች ስልጠና የመስጠት፣ በክትትልና ድጋፍ የከተሞችን አተገባበር በግብረ-መልስ የማሳየት፣ ከተሞች ባገጠሟቸው ችግሮች ላይ የመፍትሔ አማራጭ የሚያመላክቱ ጥናቶችን እና አዳዲስ የአሰራር ስርዓቶችን በማጥናት መፍትሔ እንዲወስዱ /እንዲተገብሩ/ እያስቻለ እና የተለያዩ ድጋፎችን ለከተሞች እያደረገ ይገኛል።

በከተሞች የሚመነጨው ቆሻሻ በአግባቡና ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ተይዞ ስለማይወገድ በአካባቢ ደህንነት፣ በሕብረተሰቡ ጤናና አምራችነት፣ በከርሰ ምድር ውሃ፣ በከባቢ አየርና አፈር ላይ ብክለትን እያስከተለ እና ለተለያዩ የጤና ጠንቅ የሆኑ ተሕዋስያን መፈጠር መንስኤ እየሆነ ነው። በከተሞች የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት በአግባቡ ተግባራዊ ባለመደረጉ ከተሞች ፅዱ፣ ውብና ማራኪ ሆነው ለኢንቨስትመንት ተመራጭ እንዳይሆኑ ምክንያት መሆኑንም ከጥናት መረዳት ተችሏል።

በተለያዩ ጊዜያት ከተሰሩ የክትትልና ድጋፍ የግብረ-መልስ ሰነዶች ለመረዳት እንደተቻለው በሀገራችን ከተሞች የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አስተዳደር በአግባቡ ተግባራዊ እንዳይሆን ያደረጉት ምክንያቶች ለዘርፉ የተፈጠረው መዋቅራዊ አደረጃጀት በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ወጥ ያለመሆን፣ ዘርፉ በሙያው በሰለጠነና አቅምና እውቀቱ ባላቸው አመራርና ባለሙያዎች አለመመራቱ፣ በቂ የሰው ኃይልና ግብዓት ባለመሟላቱ፣ ለዘርፉ ስራ የሚያስፈልገው በጀት አለመሟላቱ እና የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ አነስተኛ መሆኑ ዋና ዋና ምክንያቶች ናቸው።

በመሆኑም የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት ትግበራ በከተሞች ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻል ቢኖረውም በተለያዩና ከላይ በተገለፁት ችግሮች የታጠረ በመሆኑ የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት አልተቻለም። እናም የዘርፉን ውስብስብ ችግሮች ሊፈታ የሚችል የመፍትሔ እርምጃ መውሰድ እንደሚያስፈልግ መረዳት ተችሏል። ይህ የመፍትሔ አማራጭ የግል ዘርፉን በተቀናጀ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ ስራዎች ላይ ማሳተፍን መፍትሄ ያደረገ ነው።

የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አገልግሎትን ለከተማ ነዋሪው በተመጣጣኝ ክፍያ ለመስጠት፣ አገልግሎቱን ቀልጣፋ ለማድረግ እና ሁሉንም ነዋሪ በአገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ የግሉ ዘርፍ ከመንግስት በተሻለ ሚናውን መጫወት እንደሚችል የተለያዩ ነባራዊ ሁኔታዎች ያሳያሉ።

በአሁኑ ጊዜ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ የመሠረተ ልማትና አገልግሎት አቅርቦት ለማከናወን በስፋት ጥቅም ላይ እየዋለ ይገኛል። ተሳትፎውም ኃላፊነትን እና ሊፈጠሩ የሚችሉ ስጋቶችን ከመንግስት ጋራ በመጋራት ወይም ሙሉ በሙሉ በመውሰድ የሚፈጸም ነው። ጥልቅ የሆነ የአዋጭነት ጥናት መነሻ ተደርጎ እና የወጪና ገቢ ምንጩ ተገማችነት ባለው አሰራር መሰረት የሚፈጸም ተግባርም ነው። ይህም የተወሰነውን አገልግሎት በኮንትራት በመውሰድ፣ ከመንግስት ጋር በአጋርነት/በሽርክና በመስራት እና አገልግሎት አሰጣጡን ሙሉ በሙሉ በባለቤትነት በመውሰድ መስራት የሚያስችል ነው።

በተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ የግል ዘርፍ ተሳትፎ ሲባል የግል ዘርፉን ሀብት ተገማች ጥቅም በሚያስገኝ ሁኔታ መጠቀምን እና የመንግስት ፋይናንስ/በጀት ጫና መቀነስን ያካተተ ሲሆን በግሉ ዘርፍና በመንግስት በሚደረግ የጋራ ስምምነት መሠረት እና የግል ዘርፉ ላወጣው ገንዘብ ተመጣጣኝ ክፍያ በሚያስገኝ መልኩ የሚተገበር ነው።

የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራ በግሉ ዘርፍ ተሳትፎ ሲከናወን ጥቅሞች አሉት፡-

- መንግስት ያለውን ውስን የገንዘብ ሃብት ለሌሎች የልማት ፕሮጀክቶች እንዲጠቀም ያስችላል፤
- በአነስተኛ ወጪ ቀልጣፋና ተደራሽ አገልግሎት እና የቴክኖሎጂ ተጠቃሚነት እንዲኖር ያደርጋል፤
- የሚያጋጥሙ ስጋቶችን መጋራት እና/ወይም ሙሉ በሙሉ የግሉ ዘርፍ እንዲወስድ ያስችላል፤
- ተፈላጊውን የአገልግሎት ውጤት ማስገኘት ያስችላል፤ (የሚመራው ውጤትን መሰረት ባደረገ ውል ስለሆነ ክፍያ የሚፈጸመው ሕብረተሰቡ አገልግሎቱን በጥራት ማግኘቱን እና/ወይም መንግስት አገልግሎቱ በጥራት ለሕብረተሰቡ መሰጠቱን ሲያረጋግጥ እና በየጊዜው በሚረጋገጥ የአገልግሎት ደረጃ ስለሚሆን ተፈላጊውን የአገልግሎት ውጤት ያስገኛል፤)
- የረዥም ጊዜ እና አስተማማኝ መፍትሄ መሆኑ፤
- የመንግስትን አመራር ማሻሻል ያስችላል። (የግል ዘርፉ በአገልግሎቱ የቀን ተቀን ስራዎችን ሙሉ ኃላፊነት ስለሚወስድ የመንግስት ትኩረት በሌሎች የመንግስት የልማት ስራዎች ላይ ይውላል ለአብነት የክትትል፣ ድጋፍና ቁጥጥር ስራ ላይ ትኩረት ያደርጋል። የተሻሻለ የአገልግሎት ደረጃ ይፈጥራል። (መንግስት ግልጽ የሆነ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት፤ የግል ዘርፉ ደግሞ ያላቸውን ሀብት፤ ቴክኖሎጂ፤ ሀሳብ እና እውቀት በማጣመር ለሕዝብ የሚቀርበውን አገልግሎት የመስጠት ደረጃ ጥራት ይጨምረዋል፤)
- ዘርፉ አንዱ የኢንቨስትመንት አማራጭ መሆኑ፤ (የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አገልግሎት የሚሰጥበት ወጪ ሙሉ በሙሉ ወይም በአብዛኛው በመንግስት የነበረውን የወጪ ማካካሻን ተግባራዊ በማድረግ የአገልግሎት መስጠት ስራውን የግል ዘርፉ እንዲሰራው ከተደረገና የአገልግሎት ክፍያውን በመሰብሰብ ቀጣይነት ያለው ትርፋማ የሆነ ገቢ ስለሚያገኝ ስራው የኢንቨስትመንት አማራጭ እየሆነ ይሄዳል፤)
- ከፍተኛ የስራ ዕድል የሚፈጥር መሆኑ፣

ስለሆነም የግሉን ዘርፍ በተለያዩ መንገዶች በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ ማሳተፍ የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት ያስችላል።

# ነፃ ሃሳብ

## ሚዛናዊ እይታ - ለሠላም ግንባታ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ሚዛን የነገሮች ልኬት መግለጫ ነው፤ ሚዛን በማኅበረሰባችን ዘንድ ነጋዴውን ከሸማቹ፣ ባለሱቁን ከደንበኛው የሚያግባባ፣ የሚያስማማ መተማመኛ ልኬት ነው። ገበያ ወይም ሱቅ ሄዳችሁ የገዛችሁት ስኳር የተከፈለበትን ዋጋ የሚያክል መሆኑን ለማረጋገጥ ሚዛን ትጠቀማላችሁ። ግራሙና የገዛችሁት ዕቃ እኩል ሲሆን ያኔ እውነት በሆነ መንገድ ገንዘባችሁን ከፍላችሁ ዕቃችሁን ትወስዳላችሁ።

ያኔ ከሸጠላችሁ ሰው ጋር ትግባባላችሁ፤ ምክንያቱም በመካከላችሁ ሚዛኑ አለና። ግን ደግሞ ወይ ግራሙ ወይ የገዛችሁት ዕቃ ወደ አንድ ጎን አጋድሎ ከሁለት ለአንዳችሁ ካዳላ በመካከላችሁ መተማመን የለም ማለት ነው። ነገ ላይ ከዚያ ሰውዬ ዕቃ አትገዙም። ነጋዴውም ለእናንተ ለመሸጥ ፍቃደኛ አይደለም።

ይህን እውነት ወደ ሕይወት ስናመጣው እንዲህ ይሆናል። ሕይወት የብዙ አስተሳሰቦች ጥርቅም ናት። በዙሪያችን በርካታ እይታ፣ በርካታ አመለካከት ያላቸው ሰዎች አሉ። ከነሱ ጋር ነው የምንኖረው። በዚህ የጋራ ሕይወታችን ውስጥ ደግሞ የእኔ አስተሳሰብ ሌላውን እንዳይጎዳ፤ የሌላውም አመለካከት እኔን እንዳይጎዳኝ ሆነን በመቻቻል መኖር አለብን።

ልክ እንደሚዛኑ ሁሉ፣ በእያንዳንዳችን ሕይወት ውስጥ ለሌሎች የሚሆን ሚዛናዊ እውነት ሊኖረን ይገባል። ስንኖር ራስ ወዳድ በሆነ የእኔነት ስሜት ወደራሳችን ብቻ የምናተኩር ከሆነ የሌሎች ፍቅርና አብሮነት እየራቀን ይመጣል። የሌሎች ፍቅርና አብሮነት ራቀን ማለት በሕይወት ለመኖር አቅምና ጉልበት አይኖረንም።

ሚዛናዊ እይታ ለሀገር እድገት ከፍተኛ ሚና አለው። በአሁኑ ሰዓት ሀገራችን ኢትዮጵያ የተቸገረችበት አንዱና ትልቁ ነገር ሁሉን አቃፊ የሆነ ሚዛናዊ እይታ አለመኖር ነው። እይታችንም ሆነ አስተሳሰባችን አንድን ወገን ብቻ የሚጠቅም፣ ለአንድ ወገን ብቻ የሚወግን የተወሰነ ነው። ይህ የተንሸዋረረ እይታ ይባላል።

እይታችን ካልጠራ፣ አስተሳሰባችን ከወገንተኝነት ካልጸዳ ከግለሰባዊነት ባለፈ የምናመጣው ማኅበራዊ ለውጥ የለም። ምክንያቱም ለውጥ መልካም ልብ፣ መልካም ነፍስ ይፈልጋል። ብዙዎቻችን የቆምነው በሌሎች ድጋፍ ነው። አሁን ያለንበት ቦታ ለመቆማችን ብዙዎች ዋጋ ከፍለዋል። ራሳችንን ችለን የቆምን ይመስለናል እንጂ ለብቻችን የገነባነው አንዳች ሕይወት የለንም።

በዚህ ዓለም ላይ ካለሌሎች እገዛ፣ ካለሌሎች ፍቅር ራሱን ችሎ የቆመ ማንም የለም። በሕይወት ለመኖር አንዳችን ለአንዳችን እናስፈልጋለን። ብዙዎቻችን ግን ይሄን እውነት አንረዳውም። በአስተሳሰባችን፣ በንግግራችንም፣ በማኅበራዊ ሕይወታችን ሌሎችን እንደጎዳን ሌሎችን እንዳስቀየምን የምንኖር ነን።

እናም በፍቅርና በአብሮነት ለመኖር በመካከላችን የሀቅ ሚዛን ያስፈልጋል። ቅዱስ አስተሳሰብ፣ ቅዱስ እይታ ግድ ይለናል። መዝኖ ሲሰጠን ካለምንም ቅሬታ ባለሱቁን እንዳመንነው ሁሉ በማኅበራዊ ሕይወታችንም መተማመን አለብን። ካለምንም ፍራቻና ጥርጣሬ እርስ በርስ መጠጋጋት አለብን። እዚህ ምድር ላይ ለዘላለም አንኖርም። ነገን የማናውቅ እኛ፣ በትንታ የምናልፍ እኛ እርስ በርስ መጨካከንና መጎዳዳት የለብንም።

ምናልባትም ከሃምሳና ከመቶ አመት በኋላ እዚህ ምድር ላይ በሕይወት የለንም። አሁን እንኳን ብዙ እያሰቡ፣ ብዙ እያለሙ ከአጠገባችን በሕይወት የሌሉ ብዙ ናቸው። መኖር እየፈለጉ ያልኖሩ፣ ነገን ለማየት እየጓጉ ያላዩ ብዙ ወዳጆች ብዙ ቤተሰቦች አሉን። ታዲያ ስለምን እንባላለን? ስለምን ክፉና ጨካኝ እንሆናለን? መልካምነት እኮ ክፍያ የለውም። ጥሩነት እኮ ለማንም በነፃ የምንሰጠው አምላካዊ ስጦታ ነው።

አልገባንም እንጂ አሁን ላይ ዋጋ እያወጣንባቸው ያሉ ነገሮች ሁሉ የማይጠቅሙን ናቸው። የከፍታ ስፍራ መስለውን እየሄድንባቸው ያሉ ጎዳናዎች ሁሉ የሚጥሉን ናቸው። ብዙዎቻችን ሕይወትን ውስብስብ በሆነ መንገድ የምንመራ ነን። ካልተጨነቅን፣ ካልተጠበብን ካልወጣንና ካልወረድን መሸቶ የሚነጋ የማይመስለን ብዙዎች ነን። ካልዋሸን፣ ካላጭበረበርን የምንኖር የማይመስለን ሞልተናል።

> **መኖራችን ዋስትና የሚያገኘው ለሌሎች በምንሞተው ሞት ልክ ነው። ሕይወታችን ትርጉም የሚኖረው የሌሎችን ህመም በታመምነው ልክ ነው። የዚህ ዓለም መልካም ነገሮች ሁሉ በበጎ ሥራ ውስጥ የተደበቁ ናቸው። የሚያኖረን ፍቅር ነው የሚያኖረን የጋራ ሥርዓት ነው**

ሕይወት እንዲህ አይደለም፤ ምኞትና ድርጊታችን ስላልተገናኘ አብዛኛው ነገራችን ከእኛ ቁጥጥር ውጪ ነው። መልካም ሕይወት በገንዘብ ብቻ የሚመጣ የሚመስለን አለን። የምንፈልገውን ነገር ሁሉ በጭንቀታችን በኩል የምናገኝ የሚመስለን ሞልተናል። ሆኖም ካለመልካም ሃሳብ የሚሆን ምንም የለም። መኖር የምንጀምረው ለሌሎች በቆምን ለሌሎች መጨነቅ በጀመርን ማግስት ነው።

ደስታ የሚከብበን ለሌሎች ደስታን በሰጠን ሰሞን ነው። እስኪ ለአንድ አፍታ ለሌሎች መልካም በመሆን በሕይወታችን ውስጥ የሚመጣውን ለውጥ እንመልከት። እስኪ ለአንድ ጊዜ ከነበርንበት እንውጣና በሚዛናዊ አስተሳሰብ ውስጥ ራሳችንን እናግኘው። ያኔ ካለድካም ካለውጣ ውረድ መኖር እንጀምራለን። ያኔ በሕይወታችን መጥቶ የማያውቅ ሠላምና መረጋጋት የእኛ ይሆናል። ያኔ ሕይወትን እንደ አዲስ ማየት እንጀምራለን።

ይሄ ብቻ አይደለም፣ ሚዛናዊ አስተሳሰብ ከዛሬ የተሻለ ብሩህ ነገን የሚፈጥር የኃይል ክምችት ነው። አሁን ላይ እየሞትን ያለነው፣ ከስኬት ርቀን የቆምነው፣ ከድህነት መውጣት አቅቶን የምንሰቃየው በማይጠቅሙን ነገሮች ላይ ጊዜአችንን ስለምናጠፋ ነው። ከሕገ እግዚአብሔር ሸሽተን በወንድሞቻችን ላይ የጭካኔ በትር እያነሳን ያለነው የአብሮ መኖር ዋጋው ጠፍቶን ሳይሆን ጥሩ ላልሆኑ ሰዎች መጠቀሚያ ሆነን ነው።

ለሌሎች ተስፋን በመስጠት፣ ለሌሎች ቅንና አዛኝ በመሆን ቀናችንን እንጀምር። ለሌሎች የስኬት ምንጭ በመሆን፣ በየሆስፒታሉ የታመሙትን፣ በየእስር ቤቱ የታሰሩትን በመጠየቅ ሕይወታችንን ውብ ማድረግ እንችላለን። ይሄ ብቻ አይደለም ከሌላው ጋር ተግባብቶ በፍቅር መኖር ብዙ ዕድሜ የሚያኖር እንደሆነም በሳይንቲስቶች ተረጋግጧል።

ዕድሜአቸው ከመቶ አመት በላይ በሆኑ ወንድና ሴቶች ላይ የተደረገ አንድ ጥናት፣ ሁሉም አዛውንቶች በሕይወታቸው ውስጥ ለሌሎች መልካም ሥራን ያደረጉ ሆነው እንደተገኙ ተነግሯል። ሃሳባችሁ ስኬታማ እንዲሆን በመጀመሪያ ለሌሎች የስኬት ምክንያት ሁኑ። ሃሳባችሁ ከሌሎች የተሻለ ሰው መሆን ከሆነ ሌሎች የተሻሉ እንዲሆኑ መንገድ ጥረጉላቸው።

ሃሳባችን ሀገራችንን ከድህነት፣ ሕዝባችንን ከኋላቀርነት መታደግ ከሆነ ከሁሉ አስቀድመን የአብሮ መኖርን ጥበብ እንቅሰም። በሥራችን ትርፋማ ልንሆን ከሆነ ሌሎች በሥራቸው ትርፋማ እንዲሆኑ እናግዛቸው። በሕይወታችን፣ በኑሯችን እንዲሁም በትዳራችን ደስተኛ ለመሆንም ከሁሉ በፊት እንዲሆንልን የምንፈልገውን ለሌሎች እናድርግ። በዚህ ውስጥ ነው ስኬት ያለው። በዚህ ውስጥ ነው ሥልጣኔ ያለው። በዚህ ውስጥ ነው ሠላም ያለው።

የሚያስፈልገንን ከማወቃችን በፊት በመጀመሪያ ሌሎች የሚያስፈልጋቸውን ነገር እንወቅ። የምንፈልገውን ለማግኘት ከመነሳታችን በፊት ሌሎች የሚፈልጉትን እንዲያገኙ መሰላል እንሁናቸው። የእኛ የሁላችን ስኬት የሌሎችን ስኬትና ደስታ ታኮ የሚመጣ ነው። ለዚህም ነው ቅድም የሚጠቅመን እያለ ወደማይጠቅመን የምንሄድ ነን ያልኩት።

የሚያስፈልገን ነገር አጠገባችን ነው ያለው። ሁሉም ነገር ለሌሎች በሆንነው ልክ የሚሆንልን ነው። ክፋታችንና ተንኮላችን ነገን እንዳናይ ከማድረግ ባለፈ የሚሰጠን ጥቅም የለም። አባቶቻችን እኮ ያስተማሩን ፍቅርን ነው። ይቅርባይነትን ነው። እነርሱ አይደለም በጎረቤታቸውና በወንድሞቻቸው ላይ ሊጨክኑ ቀርቶ ሀገር ሊወር፣ ታሪክ ሊበርዝ የመጣውን የጣሊያን ወታደር እንኳን ማርከው በመግደል ፈንታ ውሃና ምግብ ሰጥተው በመልካም ስፍራ በማስጠለል ሕክምና የሚሰጡ ነበሩ።

መኖራችን ዋስትና የሚያገኘው ለሌሎች በምንሞተው ሞት ልክ ነው። ሕይወታችን ትርጉም የሚኖረው የሌሎችን ህመም በታመምነው ልክ ነው። የዚህ ዓለም መልካም ነገሮች ሁሉ በበጎ ሥራ ውስጥ የተደበቁ ናቸው። የሚያኖረን ፍቅር ነው የሚያኖረን የጋራ ሥርዓት ነው። ብዙዎቻችን በሕይወት የተደረገልንን መልካም ነገር አናይም። በሕይወት ውስጥ በረከት ሊያስገኙልን የሚችሉ ነገሮች በነፃ የምናገኛቸው ነገሮች እንደሆኑ ብዙዎቻችን አናውቅም።

ገንዘብ ካላወጣን፣ ካልለፋን ካልደከምን ጥሩ ነገር የምናገኝ የማይመስለን ሞልተናል። እውነቱ ግን ይሄ አይደለም፤ የደስታችን አጥቢያ ያለው ልባችን ውስጥ ነው። ለሌሎች በምንሰጠው ፍቅርና ክብር ልክ፣ ከሌሎች በምንቀበለው መልካም ምላሽ ልክ ጎዳናችን ይቀናል። ሕይወታችንን፣ አካባቢያችንን ባጠቃላይ ዓለምን የምናይበትን የአስተሳሰብ ሚዛናችንን ማስተካከል ጥሩ እንድናይ፣ ጥሩ እንናስብ ቀዳሚው ነገር ነው።

የእይታ ሚዛናችን ሳይስተካከል የምናደርገው ጉዞ ገደል ነው የሚከተን። አቻችሎና አከባብሮ አብሮ የሚያኖረንን የኢትዮጵያዊነት ወግ ሥርዓት ሽረን ባለማዕረግ አንሆንም። አሁን ላይ እዛም እዚም የምናያቸው ነውጦች፣ ሞቶች፣ መፈናቀሎች እይታቸው በተዛባ ግለሰቦች የተፈጠሩ ናቸው። ሰውነትን ባልተረዱ፣ ፈጣሪን በማይፈሩ፣ ፍቅርን በማያውቁ ጥቂት ግለሰቦች የሚፈጸም ነው።

ወደዚህ ዓለም ነፍስ እንድናጠፋ አልመጣንም። በሚያስደንቅ ፍቅር የሌሎችን ሞት እንድንሞት፣ የሌሎችን ስቃይ እንድንሰቃይ ነው ሰው የሆንነው። ወደዚህ ምድር ደም ለማፍሰስ አልመጣንም። የሌሎችን እንባ እንድናብስ፣ የሌሎችን ሲቃ እንድንገታ እንጂ። እንድንራራ፣ እንድንምር እንጂ ለጭካኔ አልተፈጠርንም። እንድንመርቅ፣ እንድናስደስት እንጂ እንድናሳዝን ሰው አልሆንም። እንድንራራ፣ ቸርነትን እንድናደርግ እንጂ እንድንበድል አልተፈጠርንም።

የብዙዎቻችን የአብሮ መኖር ሥርዓት የተሸረሸረበት ሰሞን ላይ ነን። ኢትዮጵያዊነት በዘር፣ በብሔር የተከፋፈለበት ጊዜ ላይ ነን። ወደ ስኬት እየገሰገስን፣ ወደ ልማት፣ ወደ ለውጥ እየሄድን ወደ ኋላ የምናይ ብዙዎች ነን። ኢትዮጵያ ክብሬ ናት፣ ደሜ..ማዕረጌ ብለን በአደባባይ መስክረን ዞረን ለጎዘኗ ምክንያት የምንሆን ጥቂቶች አይደለንም። የአስተሳሰብ ሚዛን መዛባት ለሀገርም ሆነ ለትውልድ የከፋ አደጋ አለው።

እንዲህ ዓይነት ማንነት ለራስ ብቻ ከማሰብ ባለፈ ለሌሎች ግድ የለውም። በየቦታው ጥላቻና መለያየትን የሚሰብክ ነው። በወንድማማቾች መካከል ጠብን የሚዘራ ነው። ዋሽቶ ከማስታረቅ ይልቅ ዋሽቶ የሚያጣላ ነው። ባልሆነና ባልተደረገ ነገር ላይ የውሸት ማስረጃ እያቀረበ ሕዝብ የሚያባላ ነው። ለእስካሁኑ ከፍና ዝቅታችን ከፍተኛውን ኃላፊነት የሚወስደው እንዲህ ዓይነቱ የራስን ይዞ የሌላውን አንጠልጥሎ ዓይነት አመለካከታችን ነው።

የአስተሳሰብ ሚዛን መዛባት መሪው እንደማይታዘዝና ፍሬኑ እንደተበጠሰ መኪና ነው። ልንራመድ እንችላለን ወዴት እንደምንሄድ ግን አናውቅም። ፍሬኑ የተበጠሰ መኪና ምን ጥቅም አለው? ገራዥ ገብቶ በባለሙያ እስካልተስተካከለ ድረስ አደጋ ከመፍጠር የዘለለ ጥቅም የለውም። ፍሬናችን አስተሳሰባችን ነው...አስተሳሰባችን ሁሉ ነገራችን ነው። ትናንታችን፣ ዛሬአችን፣ ነጋችን ሳይቀር የተገነባው በአስተሳሰባችን ላይ ነው።

በአስተሳሰባችን ላይ እክል ካለ በሕይወታችን፣ በኑሯችን በአጠቃላይ በእንቅስቃሴአችን ላይ ችግር አለ ማለት ነው። አሁኑኑ መስተካከል ይኖርብናል። አሁኑኑ ወደ ሠላም ወደ አንድነት መመለስ ይኖርብናል። ዓላማችን አንድ ሀገር፣ አንድ ሕዝብ ከሆነ ሚዛናዊ አስተሳሰብ ያስፈልገናል። ይሄ ብቻ አይደለም ሚዛናዊነት የዘመናዊነት መገለጫም ነው። ሚዛናዊነት የእውቀት፣ የጥንካሬ ከሁሉ በላይ የሰውነት መገለጫ ነው።

እስኪ ራሳችንን እንፈትሽ፤ ምን ዓይነት ሰዎች ነን? ምንድነው የምናስበው? ለሀገርና ሕዝብ የሚሆን ምን ጥሩ ነገር አለን? ምርጥነታችን ያለው በእነዚህ ጥያቄዎች ውስጥ ነው። አንድ ነገር ሁሌም አስታውሱ ሃሳባችን ድርጊታችንን፣ ድርጊታችን ማንነታችንን ይገልጸዋል። ማናችንም ደግሞ በክፉ ማንነት መታወስ አንሻም። ያ እንዳይሆን ሚዛናዊ እሳቤን ልንለማመድ ይገባል።

ጨዋነት ክፉ ሆኖ አያውቅም። የሠላም ሁሉ ስፍራው ተነጋግሮ መግባባት ነው። ተነጋግሮ መግባባት አንዱና ዋነኛው የጨዋነትና የሚዛናዊነት መነሻ ነው። እንደሀገር እያስተናገድናቸው ያሉ መከራዎች እንዲያበቁ በጨዋነት መነጋገርን እንልመድ። እንዲህ ካልሆነ የነበረው እንደባሰ ሁሉ ያለውም ብሶ ይቀጥላል።

የአብዛኞቻችን ማንነት በስሜት የተገነባ ማንነት ነው። ለዛም ነው ከሠላም ይልቅ ለጦርነት፣ ከእርቅ ይልቅ ለመለያየት የምንፈጥነው። ሚዛናዊ ሃሳብ ባለበት አእምሮ በኩል ሀገራችንን ካልገነባናት በምንም ብንገነባት ልክ አትሆንም። እየካብን የሚናድብን፣ እየገነባን የሚፈርስብን መሠረቱ ሚዛናዊ ሃሳብ ስላልሆነ ነው።

ሕይወትን በእውነትና በምክንያት መኖር አንዱና ዋነኛው የሚዛናዊ ጭንቅላት መገለጫ ነው። ሁላችንንም በሚያስማማ መልኩ ምርጥነት ለሌሎች መትረፍ፣ ሌሎችን ማፍቀር፣ ሌሎችን መረዳት ነው። ምርጥ ሰዎች ምርጥ ነገር የሚያስቡ ናቸው። በየትኛውም እውቀት በየትኛውም መመዘኛ ብታዩት ምርጥነት ከዚህ የዘለለ ትርጉም የለውም። ነገ ለምትፈጠረው ኢትዮጵያ በሚዛናዊነት የተቃኘ ሁሉን አቃፊ አስተሳሰብ ያስፈልገናል። የሁላችን የጋራ ቤት የሆነችውን አዲሲቷን ኢትዮጵያ ለመገንባት ከአሮጌነት እንውጣ። ለሠላማችን ሚዛናዊነትን እንላበስ።

# 116ኛው
# የሀገር መከላከያ ሰራዊት ቀን
## አከባበር በመስቀል አደባባይ














ፎቶ፡ አዮብ ተፈሪ እና በሪሁን ታደለ

# ስፖርት





# የሉሲዎቹ የኦሊምፒክ ጉዞ በአቡጃው ፍልሚያ ይወሰናል



ሉሲዎቹ በኦሊምፒክ ማጣሪያ የመልስ ጨዋታቸውን የፊታችን ማክሰኞ በአቡጃ ያደርጋሉ፣

**ብርሃን ፈይሳ**

አፍሪካ በሁለት ቡድኖች ለምትወከልበት ኦሊምፒክ እግር ኳስ የአህጉሪቱ የሁለተኛ ዙር ማጣሪያ የመልስ ጨዋታዎች ከቀናት በኋላ ይደረጋሉ። የመጀመሪያውን ዙር የማጣሪያ ጨዋታ በሜዳው ከናይጄሪያ ጋር በአቻ ውጤት ያጠናቀቀው የኢትዮጵያ ሴቶች ብሔራዊ ቡድን (ሉሲዎቹ) ወደቀጣዩ ዙር ለማለፍ የሚያስችለው እድል አጣብቂኝ ውስጥ የገባ ቢሆንም የፊታችን ማክሰኞ አቡጃ በሚካሄደው የመልስ ጨዋታ ይፋለማል።

በ2024ቱ የፓሪስ ኦሊምፒክ ለመሳተፍ ሁለተኛ ዙር የማጣሪያ ውድድራቸውን እያደረጉ የሚገኙት ሉሲዎቹ ከትናንት በስቲያ በአበበ ቢቂላ ስቴድየም ናይጄሪያን ገጥመው 1ለ1 በሆነ አቻ ውጤት መለያየታቸው ይታወቃል። በሜዳቸው በአህጉሪቱ ጠንካራ የሆነውን የናይጄሪያ ቡድንን የገጠሙት ሉሲዎቹ በጨዋታው ነጥብ መጋራታቸው በቀጣይ የሚኖራቸውን የማጣሪያ ጉዞ ከባድ አድርጎታል።

በጨዋታው ሉሲዎቹ በአውሮፓ ታላላቅ ሊጎች በሚጫወቱ ከዋክብት የተሞላውን የናይጄሪያ ሴቶች ብሔራዊ ቡድን (ጭልፊቶቹን) ብርቄ አማረ 5ኛ ደቂቃ ላይ ባስቆጠረችው ግብ መምራት ቢችሉም፣ ከእረፍት መልስ 51ኛ ደቂቃ ላይ የስፔኑ አትሌቲኮ ማድሪድ ኮከብና የጭልፊቶቹ አምበል የሆነችው ራሺዳት አጂባዴ በሉሲዎቹ ግብ ጠባቂ ታሪኳ በርገና መረብ ላይ ያሳረፈቻት ድንቅ ግብ አቻ አድርጋለች። ሁለቱ ቡድኖች በቀሪዎቹ 40 ደቂቃዎች ኳስና መረብ ሳያገናኙም ጨዋታው በአቻ ውጤት ተጠናቋል። በኦሊምፒክ መድረክ የሶስት ጊዜ የተሳትፎ ታሪክ ያላት እንዲሁም በቅርቡ ዓለም ዋንጫ ላይ ተካፋይ የነበረችው ናይጄሪያ ለሉሲዎቹ ፈተና ይሆናሉ በሚል ይጠበቁ ነበር። ነገር ግን እንደተጠበቀው በናይጄሪያዊያኑ በኩል የተለየ ብልጫ ማሳየት አለመቻላቸው ታይቷል። በተለይ የቀድሞዋ የሊቨርፑል፣ አርሰናል እና አሁን የባርሴሎና ተጫዋች የሆነችው አሲሳት ኦሾላ በጨዋታው የጭልፊቶቹ ልዩነት ፈጣሪ ትሆናለች ተብሎ ቢጠበቅም፣ ብቸኛዋ የአፍሪካ የባሎን ድ ኦር ሽልማት እጩ በጨዋታው ምንም መፍጠር አለመቻሏ ታይቷል።

በሜዳና በደጋፊያቸው ፊት የነበራቸውን እድል ያልተጠቀሙት ሉሲዎቹ በተደጋጋሚ የግብ ዕድሎችን መፍጠር ቢችሉም ኳስና መረብ ማገናኘት ባለመቻላቸው ሙሉ ነጥብ ማሳካት ተስኗቸዋል። ከቀናት በኋላ በሚኖራቸው የመልስ ጨዋታም ላይ የተለየ ስልት ይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል። ጨዋታውን ተከትሎም የቡድኑ ዋና አሰልጣኝ ፍሬው ኃይለገብርኤል፣ ሁለቱም ቡድኖች በጫና ውስጥ ሆነው የተጫወቱ ቢሆንም ጭልፊቶቹ ያላቸውን ልምድ ተጠቅመው ነጥብ ሊጋሩ መቻላቸውን ከጨዋታው በኋላ በሰጡት አስተያየት ተናግረዋል። ከእረፍት በኋላ ቡድኑ የነበሩበትን ክፍተቶች አርሞ ወደ ጨዋታ ቢመለስም በተጫዋቾች በኩል ችኮላ ባይኖርባቸው የተሻለ ነገር ማድረግ ይቻል እንደነበር አሰልጣኙ ገልፀዋል። ለመልሱ ጨዋታም ከመጀመሪያው ጨዋታ በመነሳት የተለየ ዕቅድ እንደሚያዘጋጁም አሰልጣኙ ጠቁመዋል።

የጭልፊቶቹ ዋና አሰልጣኝ ጀስቲን ማዱጉ በበኩላቸው ነጥብ ይዘው ለመውጣት አቅደው ቢጫወቱም፤ በሉሲዎቹ በኩል በገጠማቸው ጠንካራ ፍልሚያ እንዲሁም ጥራት የሌላቸውና ደካማ ኳሶች ምክንያት ነጥብ መጋራታቸውን ገልጸዋል። በቀጣዩ ጨዋታም ይህንኑ አርመው እንደሚገኙና ውጤት እንደሚያስመዘግቡም አመላክተዋል።

የሁለቱ ቡድኖች የመልስ ጨዋታ ማክሰኞ ጥቅምት 20/2016 ዓ.ም አቡጃ ላይ የሚካሄድ ሲሆን ሉሲዎቹ ከሜዳቸው ውጪ ከባድ ፍልሚያ የሚጠብቃቸው ይሆናል። ሉሲዎቹ በደርሶ መልስ ድምር ውጤት ማሸነፍ ከቻሉ በቀጣዩና ሶስተኛው ዙር ማጣሪያ ከካሜሩንና ዩጋንዳ አሸናፊ ጋር ይገናኛሉ።

ሁለት የአፍሪካ ቡድኖች በሚሳተፉበት ኦሊምፒክ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ለማለፍ በአሰልጣኝ ፍሬው ኃይለገብርኤል የሚመሩት ሉሲዎቹ ከቀናት በኋላ ወደ ናይጄሪያ ያመራሉ። 11 ጊዜ የአፍሪካ ዋንጫን በማንሳት ትልቅ ስም ያላቸው ጭልፊቶቹ በዓለም ዋንጫ ተከታታይ ተሳትፎ ያላቸው ሲሆን፤ እአአ በ2000 እና 2004 በኦሊምፒክ መድረክ ተሳታፊ እንደነበሩ ይታወቃል። በ2004 የአቴንስ ኦሊምፒክ ተሳትፏቸውም እስከ ሩብ ፍጻሜ ሲጓዙ ከቤጂንግ ኦሊምፒክ በኋላ ግን በመድረኩ አልተካፈሉም። በመሆኑም ጭልፊቶቹ በፓሪሱ ኦሊምፒክ ተሳታፊ ለመሆን ከፍተኛ ጥረት እንደሚያደርጉ ይጠበቃል።


## አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም ኢስት አፍሪካ ቦትሊንግ አ.ማ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-29537 የተሽከርካሪው አይነት ተሳቢ የሻንሲ ቁጥር EADBDAMMTH0000039 ሞዴል DRAWBAR የሞተር ቁጥር Trailer የሊብሬ ቁጥር 0195327 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ8/2/2016 ዓ.ም. አመልክተዋል፡፡
ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ልደታ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም መስከረም ጌታቸው ደገፋ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-B69886 የተሽከርካሪው አይነት አነስተኛ አውቶቡስ (ከ12 ያነሰ መቀመጫ) የሻንሲ ቁጥር DA52V-165451 ሞዴል GD-DA52V የሞተር ቁጥር F6A-IL280256 የሊብሬ ቁጥር 236218 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ13/2/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይገኛለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ልደታ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ንግስቲ ተከስተ በርሄ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-C21576 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር SCP11-0066941 ሞዴል UA-SCP11-BEMNK-L የሞተር ቁጥር 1SZ-1069954 የሊብሬ ቁጥር 461061/461790 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ9/2/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይገኛለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ቦሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ያእቆብ ወ/መስቀል ኮስትሬ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-A36693 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር KSP90-50056202 ሞዴል DBA-ksP90L-AHXNK የሞተር ቁጥር 1KR-0092759 የሊብሬ ቁጥር 265175 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ13/2/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይገኛለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ንፋስ ስልክ ላፍቶ ቅ/ጽ/ቤት**

## የጨረታ ማስታወቂያ

**የጨረታ ቁጥር DCE/SF/150/2023**

የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ ለጃንሜዳ G+3 ፕሮጀክት አገልግሎት የሚውል "Supply, and fix Audio Visual System Including all mounting and operational necessary accessories" ግዥ ለመፈፀም ተጫራቾችን በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

| N.o. | የዕቃው ዓይነት | ፕሮጀክት | የጨረታ ቁጥር | የጨረታው መዝጊያ ቀን እና ሰዓት | የጨረታው መከፈቻ ቀንና ሰዓት | የጨረታ ማስከበሪያ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | "Supply, and fix Audio Visual System Including all mounting and operational necessary accessories | ለጃንሜዳ G+3 ፕሮጀክት | DCE/SF/150/2023 | ህዳር 6/2016 ከሰዓት 8፡00 ሰዓት | ህዳር 6/2016 ከሰዓት 8፡15 ሰዓት | 100,000 ብር |

**ስለሆነም፡-**

1. የተጫራቾች ህጋዊነት ለማረጋገጥ የሥራ ዘርፉን የሚያሳይ የታደሰ የንግድ ፈቃድ፣ የዘመኑን ግብር የከፈሉበት ከግብር ሰብሳቢው ባለሥልጣን የሚሰጥ የታደሰ ታክስ ክሊራንስ፣ የግብር ከፋይ ሰርተፊኬት፣ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት፣ የአቅራቢዎች ዝርዝር ላይ ስለመመዝገባቸው ማስረጃ ሊሆን የሚችል መረጃ እና ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገቡበትን ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡
2. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ከታወቀ ባንክ የተረጋገጠ (CPO) ወይም ከታወቀ ባንክ በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና (Unconditional Bank Guarantee) የ100,000 ብር /አንድ መቶ ሺህ ብር/ ከመጫረቻ ሰነድ ጋር ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
3. አንድ ተጫራች መወዳደር የሚችለው በአንድ ዓይነት ምርት /ብራንድ/ ብቻ ነው፡፡ በአማራጭ የቀረበ ዋጋ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡
4. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ ብር 200.00 /ሁለት መቶ ብር/ በመክፈል ዘወትር በሥራ ሰዓት ወሎ ሰፈር አካባቢ በሚገኘው የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ ዋናው መ/ቤት የግዥና አቅርቦት አስተዳደር መምሪያ ቢሮ መግዛት ይችላሉ፡፡
5. ተጫራቾች የሚወዳደሩበትን የጨረታ ቴክኒካል ሰነድ እና ዋጋ በታሸገ ኤንቨሎፕ ከላይ በሰንጠረዡ በተገለፀው ቀንና ሰዓት በኢንተርፕራይዙ የግዥና አቅርቦት አስተዳደር መምሪያ ቢሮ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
6. ኢንተርፕራይዙ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፡፡

**አድራሻ፡-**
**የቀጥታ ስልክ ቁጥር 011 440 34 34**
**ማዞሪያ 0114-42-22-70/71/72**
**ፖ.ሳ.ቁ. 3414 ፋክስ ቁ. 0114-40-04-71/0114-42-07-46**
**ወሎ ሰፈር የቀድሞው ኖሬላ ግቢ**
**ድረ-ገፅ WWW.dce.et.com**
**ኢሜል- INFO @ dce-et.com**

## የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ